# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ

# የመድሀኒት አቅርቦት አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 63/2013

**ጥቅምት 2011**

**አዲስ አበባ**

**መግቢያ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ተቋማት የመድኃኒት አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት መወሰኛ ደንብ ቁጥር 74/2008 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሰጠው ስልጣን

መሰረት መውጣቱ ይታወሳል፤ ደንቡ ሲወጣ ያደረጋቸው ታሳቢዎች መካከል የመድኃኒት አጠቃቀምና አያያዝን በሚመለከት የሚያጋጥም የጥራት ችግር እና ብክነትን ለመከላከል እንዲያስችል፤ለመድኃኒት አስተዳደር የሚያገለግሉ ሰነዶች ግልፅነት እንዲኖራቸው፤ኦዲትእና ቆጠራ ለማከናወን እንዲያመች፤ የጤና ተቋማት የፋይናንስ አቅም ለማሳደግ፤ መሰረታዊ መድኃኒቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ ለማቅረብ እንዲያመች በማስፈለጉ ነው፡፡

ይህንን መነሻ በማድረግ በከተማ አስተዳደሩ ስር ባሉ የጤና ተቋማት እየተስተዋሉ ያሉትን የመድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም ብክነት ለመቀነስና ብሎም ለማስወገድ እንዲያመች፣የመድኃኒት ክምችት ያለባቸው ተቋማት ላይ እጥረት ወደገጠማቸው ተቋማት በዝውውር የሚገለገሉበትን አሰራር በግልፅና በህግ የተደገፈ አሰራርን ማስቀመጥ በማስፈለጉ፣ በዕርዳታ ገቢ የሚሆኑ መድኃኒቶች ለብልሽ አሰራርና ለሙስና በር እንዳይከፍቱ ግልፅ የሆነ አሰራር ማስቀመጥ በማስፈለጉ፤

የጉድለት ተጋላጭነት ማካካሻ አፈፃፀም መመሪያ በማስፈለጉ፣ የመድኃኒት አገልግሎት አሰጣጡ ስርዓት በሚገባ እንዲመራ እና ተጠያቂነት ያለበት አሰራርና የተደራጀ የሰው ኃይል የያዘ አደረጃጀት ማስቀመጥ በማስፈለጉ፣ አገልግሎት ላይ የማይውሉ የመድኃኒት አወጋገዱ ስርዓትና በሀገር አቀፍ ደረጃ በወጣው ህግ መሰረት መፈፀም በማስፈለጉ፣የቅድመ መድኃኒት ግዢ ዕቅድ ዝግጅት ፣ አቅርቦት፣ክምችትና አያያዝ፣ስርጭት፣ሽያጭና አወጋገድ ስርዓት እንዲሁም መድኃኒት አጠቃቀምና አገልግሎት አሰጣጥ ሥነ-ምግባር በግልፅ ማስቀመጥ በማስፈለጉ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ደንብ ቁጥር 74/2008 አንቀጽ 28 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

## 1. አጭር ርእስ

***ይህ መመሪያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ እና በስሩ የሚገኙ ጤናተቋማት የመድሀኒት አቅርቦትና የፋርማሲ አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 63/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡***

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. «**የጤና ተቋም**» ማለት ለህብረተሰቡ የጤና አገልግሎት የሚሰጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ስር □ሚተቴ□ር □መንግስት ተቋም ነው፡፡
2. "**የጤና አገልግሎት**" ማለት የሰውን ልጅ ጤንነት ለመጠበቅ የሚደረግ በሽታን ለመከላከል፣ ለመመርመር፣ ለማከም፣ ለመምከር እና የፋርማሲ አገልግሎት የመስጠት ተግባር ነው፡፡
3. «**□ኛርማሲ አገልግሎት** » ማለት በጤና ተቋማት ውስጥ ፈቃድ ባለው የመድሃኒት ባለሙያ የሚከናወን የእለት ተእለት የስራ እንቅስቃሴ ሲሆን አቅርቦትን፤ ክምችትን፤ ስርጭትን፤ ቅመማን፣ □ሽያጭና □ደላን፤ የምክር አገልግሎትን፤ ሰነድ አያያዝን፣ የመረጃ አገልግሎትንና ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትንም ያካትታል፡፡
4. «**መድሃኒት**»ማለት በሽታን ለመመርመር፣ ለመከላከል፣ ለማስታገስ ወይም ለማከም የሚያገለግል ማንኛውም ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ውህድ ሲሆን የህክምና መገልገያ- ችንና □ሕ□ምና መሳሪጸ- ችን □ፊ ምራል፡፡
5. «**የሕክምና መሳሪያ**» ማለት የሰውን በሽታ ለመመርመር ወይም ለማከም በውስጥ ወይም በውጭ አከል ላይ ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም መሳሪያ ወይም መገልገያ ሲሆን የተለያዩ የመመርመሪያ የላቦራቶሪ፣ የቀዶ ህክምና፣ የጥርስ ህክምና መሳሪጸ- ች፣ □እንዲሁም ለላቦራቶሪ፣ ለራጅ እና ለድንገተኝ ክፍል አገልግሎት የሚውሉ የተለየዩ ማሽኖች፣ አልጋ- ች፣ ስትሬቸር፣ ዊልቸሮች፣ □□ም ግፊት መለኪያና መሰል መሳሪጸ- ችን እና መገልገያ- ችን ያካትታል፡፡
6. «**የሕክምና መገልገያ**» ማለት በሽታን ለመመርመር ወይም ለማከም በውስጥ ወይም በውጭ የሰውነት አካል ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም መገልገያ ሲሆን የቁስል መርፌ- ችን፣ ኛሻ፣ □□፣ ጓንቶችን፣ ሲሪንጆችን፣ ጥጥና መሰል ዝግጅቶችን ሰው ሰራሽ ጥርሶችን፣ ኬሚካሎችን የጨረር ፊልሞችንና መሰል መሳሪያ- ችን እና መገልገያ- ችን □ፊ ምራል፡፡
7. «**የጅንስ ስም**» ማለት በንግድ ስም ጥበቃ የማይደረግለት አጭር የኬሚካል ስያሜ ነው፡፡
8. «**የናርኮቲክ መድሃኒቶች ወይም ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች**» ማለት ኢትዮጵያ በተቀበለችው የተባበሩት መንግስታት የናርኮቲክ መድሃኒቶች ወይም የሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች ቁጥጥር ስምምነት መሰረት አለም አቀፍ ቁጥጥር የሚካሄድበት መድሃኒት ሲሆን የሚመለከተው አካል የናርኮቲክ ወይም የሳይኮትሮፖክ መድሃኒት ብሎ የሚያወጣቸውንም ይጨምራል፡፡
9. «**የቅዝቃዜ ሰንሰለት**» ማለት አምራቹ አካል ባስቀመጠው መስፈረት መሰረት የቅዝቃዜው መጠን ክትትል የሚደረግበት የመድሃኒት ቅብብሎሽ ሂደት ነው፡፡
10. «**የመድሀኒት ማዘዣ ወረቀት**» ማለት ፈቃድ ባለው የሕክምና ባለሞያ የሚጻፍና በመድሀኒት ባለሙያ ተተርጉሞ መድሀኒትን ከበቂ መረጃ ጋር ለህሙማን ለማደል የሚያገለግልና ለዚሁ አላማ ተብሎ በተገቢው አካል ደረጃ ወጥቶለት የተዘጋጀ ህጋዊ የመድሃኒት የማዘዣ ወረቀት ነው፡፡
11. «**የመድሀኒት ተደራሽነት**» ማለት ጥራታቸውን የጠበቁ አስፈላጊ መድሃኒቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ቀጣይነት ባለዉ መልኩ በተፈለገበት ቦታና ጊዜ ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ማቅረብ ማለት ነው፡፡
12. «**□መፅ□ ኻፉ**» ማለት በመድኃኒት አቅራቢዎች ወ□ም ክርቴ□ሠቸ ዖቾ ሰነድ ላይ የሰ□ረዉ የመድሀኒት ዋጋ ማለት ሲሆን በእርቴ□ለሚመጡና በሰነዳቸው ላይ ዋጋቸው ያልተቀመጠላቸዉ መድሀኒቶች በተቋሙ ባለሙያ- ች □ሚተመንላቸው ኻፉ ማለት ነው፡፡
13. «**□ነጠላ መሸ□ ኻፉ**» ማለት የነጠላ ወይም የአንድ እሽግ የመድሀኒት የመግዣ ዋጋ ላይ ከ20ን ያልበለጠ

የትርፍ ምጣኔ በመጨመር ጤና ተቋሙ መድሀኒቶችን □ሚሸዓበት ዥፉ ነው፡፡

14. «የችርቻሮ ዋጋ» ማለት ከነጠላ የመድሃኒት ዋጋ በመነሳት የሚሰላ ሲሆን መድሀኒቱን ጤና ተቋሙ በሽጸ□ ለተ□ቃሚው □ሚያስተላለፍበት የቅንጣት ወይም የመጨረሻ ትንሹ የመጠን መለኪያ ዥፉ ነዉ፡፡
15. የመድሀኒት ቅብብሎሽ ማለት የተፈቀደ መድሀኒትን በተፈቀደለት የመድሀኒት ባለሙያ፣ ከህጋዊ አቅራቢ፣ የሙያ ደረጃው በሚፈቅደው መልኩ፣ ደህንነትን በጠበቀ አያያዝ፣ ህጋዊ የአቅርቦት ሰንሰለቱን ተከትሎ ወደ ጤና ተቋማት ማስገባት፣ ወደ ልዩ ልዩ ክፍሎች ማውጣት/ማሰራጨት እና ለህሙማኑ በተገቢው መንገድ ማስተላለፍ ማለት ነው፡፡
16. የመድሀኒት ዝውውር ማለት የአገልገሎት ጊዜያቸው በመቃረቡ፣ ምክንያት ወይም ከፍላጎት በላ□ በክምችት በመኖራቸው ወይም ድንገተኛ የመድሀኒት ዕጥረት ሲያጋጥም በጤና ተቋማት መካከል ህግን ተከትሎ መድሀኒትን አዘዋውሮ አገልግሎት ላይ እንዲውል □ማትረፅ ተፅባር ማለት ነው፡፡
17. «ህገወጥ የመድሃኒት ዝውውር» ማለት መድሃኒትን ባልተፈቀደለት ሰው ወይም ካልተፈቀደ ምንጭ ወይም የሙያ ደረጃው በማይመጥን ሰው ወይም ደህንነቱ ባልተጠበቀ አያያዝ ወይም በማንኛውም ከህግ በሚጻረር አኳኋን ህብረተሰቡን በሚጎዳ መልኩ ያልተገባ ጥቅምን ለማግኘት የሚደረግ ህገወጥ የመድሃኒት ስርጭት ማለት ነው፡፡
18. «□ክርቴታ የተገኘ መድሀኒት» ማለት ከተቋሙ በጀት ውጭ የሆኑና ከተለያዩ ድርጅቶች በነፃ ለጤና ተቋሙ የሚለገስ መድሀኒት ነው፣
19. «ከክፍያ ነጻ የሆኑ መድኃኒቶች» ማለት በዕርዳታ የተገኙ ወይም በበጀት የተገዙ መድሀኒቶች ሆነው መንግስት በነፃ እንዲስተናገዱ ለወሰናቸው የህክምና አገልግሎት ዓይነቶች ያለክፍያ ለተጠቃሚው የሚታደሉ መድሃኒቶች ናቸው፡፡
20. «የመድሀኒት ባለሞያ» ማለት አግባብ ባለው አካል በየደረጃው የሙያ ፈቃድ የተሰጠው ፋርማሲስት፣ ድራጊስት፣ ወይም ፋርማሲ ቴክኒሽያን ማለት ነው፡፡
21. «□መትኃኒት የምርት መለያ ቁዓር» ማለት በአንድ የምርት ሂደት ወቅት የተመረቱ መድሀኒቶችን ለመለየት በአምራቹ ድርጅት የሚሰጥና በማሸጊጸዉ ላ□ እና በግዥ ወይም የእርዳታ ዝርዝር ሰነዱ ላይ በግልጽ የሚፃፍ ቁጥር ነው፡፡
22. «የመድሀኒት የውስጥ መለያ ቁጥር» ማለት የእያንዳንዱን የመድሃኒት አይነቶች እንቅስቃሴ ለመከታተል አመቺ እንዲሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ ወየም በጤና ተቋሙ የሚሰጥ መለያ ሲሆን የግብይቱን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ጤና ተቋሙ በተጨማሪ የሚሰጠውን መለያ ቁጥር ይጨምራል፡፡
23. «ቆ□ራ»ማለት በተቋሙ ዉስዓ □ሚቶኘውን መድሀኒት በአይነት፣ በመጠን፣ በዋጋ፣ በመጠቀሚያ ጊዜና በመድሀኒት የውስጥ መለያ ቁጥር ለይቶ በማስቀመዓ በአካል □መቁ□ር ተግባር ነው፡፡
24. «የተስተካከለ የቀን □መትሃኒት ሽያጭ» ማለት በቀን ሽያጭ አማካይነት ከተሰበሰበው ገንዘብ ውስጥ በማስበለጥም ሆነ በማሳነስ የተሸጡትን መድኃኒቶች በመመርመር፣ የአገልግሎት ዋጋን ሳይጨምር፣ በቀን የተሸጠው የመድሀኒቱ ትክክለኛ ዋጋ ለብቻ ተለይቶ የሚገኝ ሽያጭ ነው፡፡
25. "የክሊኒካል ፋርማሲ አገልግሎት" ማለት ትክክኛ የመድኃኒት አጠቃቀምን ለማረጋገጥ ፋርማሲስቶች በአስተኝቶ ማከምና በተመላላሽ እና ድንገተኛ ህክምና አሰጣጥና የክትትል ሂደቱ ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ በመሆን፣ ህሙማኑ ካላስፈላጊ □መትሃኒት ወጪ እና ፈውስን ከማግኘት አንጻር የላቀ ተጠቃሚ እዲሆኑና መከላከል ከሚቻል □መትሃኒት ጉዳት በጸዳ መልኩ የሚፈለገውን የህክምና ውጤት ለማግኘት የሚያስችል የፋርማሲ የአገልግሎት ዘርፍ ነው፡፡
26. «□በሽታ አምጭ ተህዋስያን ከጸረ-ተህዋስያን መድሃኒቶች ጋር መላመድ» ማለት በሽታ አምጪ ተህዋሲያን (ባክቴሪያ፣ ቫይረስ፣ እና ፕሮቶዞዋ የመሳሰሉት) ከመድሃኒቶች ጋር በመላመዳቸው የተነሳ የመድሀኒቶች በሽታን የመፈወስ አቅም ወይም ፍቱንነት መቀነስ ወይም ማጣት ነው፡፡
27. «የአገልግሎት ዘመን ማብቂያ ቀን» ማለት አንድ መድኃኒት በተገቢው አቀማመጥ ሆኖ የይዘት ለውጥ ሳያመጣ ሊቆይ የሚችልበት ጊዜ ተብሎ በአምራቹ ድርጅት የተቀመጠለት ቀን ሲሆን በመድሀኒቱ ማሸቿጸ ላ□ በፅል□ □ተጻፈ ነው፡፡
28. «ጥቅም ላይ የማይውሉ መድሀኒቶች» ማለት የተበከሉ፣ በተገቢው ሁኔታ ያልተቀመጡ፣ አላግባብ የተከፈቱ፣ የቀዝቃዛ ሰንሰለት ያልጠበቁ፣ በተገቢው አካል ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የተከለከሉ፣ የአገልግሎት ዘመን ማብቂያ ቀናቸው ያለፈባቸው እና በሌሎች ምክንያቶች የይዘት ለውጥ ያስከተሉና ለሰው ጤና አደገኛ የሆኑ መድሀኒቶችን ማለት ነው፡፡
29. «□□ፀ በ□ፀ ሽጸ□ »ማለት የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ባወ□ዉ ህፉዊ □ረሰኝ ታከሚዉ ለ□□ለተ መትሃኒት ገንዘብ ከፍሎ □ረሰኝ □ሚወስትበት አገልፅሎት ነው፡፡

30. "ኤ ፒ ቲ ኤ ስ" ማለት ለኦዲት ምቹ የሆነ የፋርማሲ አገልግሎት ሲሆን በፋርማሲ አገልግሎት ወጥስ ግልጸኝነት፤ ተጠያቂነት፤ ለታካሚዎች ምቹና ቀልጣፉ የሆነ የፋርማሲ የአሰራር ስርአት ነው፡

**31.** "**የአስፈጻሚ አካላት**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ፣ የክፍለ ከተማና ወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች እና ጤና ተቋማትን ያካትታል፡፡

**32.** "**ቢሮ**"ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ነው፡፡

**33.** "ደንብ"ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ተቋማት የመድኃኒት አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት መወሰኛ ደንብ ቁጥር 74/2008 ነው፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ፣ **ክፍለ ከተማ** ጤና ጽ/ቤቶች እና በቢሮው ስር በሚተዳደሩ □መንግስት ጤና ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

# ክፍል ሁለት

## የአስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር

### 4 . የቢሮ ተግባርና ሀላፊነት

1. የመድኃኒት አገልግሎትን በተመለከተ የወጣዉን ሀገር አቀፉ የጤና ተቋማት ደረጃ በተሟላ ሁኔታ እዲተገበር ለጤና ተቋማት ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ክትትል ያደርጋል።
2. የጤና ተቋማት የመድሀኒት በጀት አቅም የሚጎለብትበትን ሁኔታ ያመመቻቻል።
3. የመሰረታዊ መድኃኒቶች አቅርቦት እና የአገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ጥናቶች ያካሂዳል፣ እንዲካሄዱ ያደርጋል፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል።
4. በመንግሰት ግዥና ንብረት አስተዳደር □ሊሲ- ች፤ ህጎች፤ መርሆ- ችና □አፈፃፀም መመሪጸ- ች መሰረት ስለመድሀኒት አቅርቦትና ስርጭት አመራር ይሰጣል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ □ቆ□□ራል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም □ማስተካከያ እርምጽ □ወስቴል።
5. ከፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጋር በመመካከር ለመድሀኒት አገልገሎት አሰጣጥ አመች የሆኑ የገቢ፣ □ወቻ ና □ሽጸ□ መሰብሰቢጸ ደረሰኞች እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ቅጻቅጾችና መዝገቦች እንዲዘጋጁና ስራ ላ□ እንዲውሉ ጸ□ርፉል።
6. የመድሀኒት ስራ አመራሩን በተመለከተ ለመድሀኒት ባለሞያ- ችና ሌሎች ፈፃሚ አከላት የሙያና የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል፤ የአሰራርና አደርጃጀት ስርአት በመዘርጋት አፈፃፀሙን ይከ□ተላል።
7. የመድሀኒት አቅርቦት፣ስርጭት፤አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ለመከታተል ያመች ዘንድ በየጤና ተቋማቱ የመደሀኒትና ሕክምና መማክርት ኮሚቴ እንዲቋቋምና ሀላፊነቱን እንዲወጣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል። አፈፃፀሙን □ከ□ተላል።
8. በጤና ተቋማት ውስጥ ከፍ□ተ በላይ ሆነው የተከማቹ መድሀኒቶች በሚኖሩበት ጊዜ የመድሀኒት እጥረት ወዳለባቸው ሌሎች የጤና ተቋማት ተዛውረው አገልግሎት ላይ እንዲ□ሉ አመራር □ሰ□ል
9. የአገልግሎት ዘመናቸው ጸለ□ና በልዩ ልዩ ምክንያት ጥቅም ላይ የማይውሉ መድሀኒቶች ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው የአወፉቶት መመሪያ መሰረት መወገዳቸውን ይከታተላል።
10. ለመድሀኒት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያገለግል የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት ይዘረጋል፣ ድጋፍና ክትትል ጸ□ርፉል።
11. በጤና ተቋማት ውስጥ ገቢና ወጭ ሆነው ወደተለያዩ ክፍሎች የሚሰራጩ መድሀኒቶች ለተጠቃሚው በትክክል መድረሳቸውን እና የተገልጋይ እርካታ የሚያረጋግጥበትን የአሰራር ስርዓት በተቋማት □□እንዲተገበር ድጋፍና ክትትል ያደርጋል።
12. በመድሀኒት አገልግሎት አሰጣጥና ሥርጭት ተግባር ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞችና ባለሙያ- ች □ክዝና መጠበቂያና የጉድለት ተጋላጭነት ማካካሻ መመሪጸ እንዲወ□ ጸ□ርፉል።
13. በጤና ተቁማት የመድሃኒት አቅርቦት እና አጠቃቀም እንዲሁም □አገልግሎት አሰጣዓ በዉስዓ ኦዲት በ□ሩብ □መቱ እና በውጭ□ ኦቴተር ቢያንስ በአመት አንድ ቴ□ መከናወኑን ጸረፉፅ□ል።
14. በጤና ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ መሰረት የህክምና መሳሪዎች ስፔስፊኬሽን ያዘጋጃል፤የአጠቃቀም ስልጠና ይሰጣል፤ ቅድመና ድህረ ጥገና ያከናውናል እንዲሁም ድጋፍና ክትትል ያደርጋል።
15. በአመት አንድ ጊዜ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን መድኃኒቶች መወገዳቸውን ያረጋግጣል፡፡

## 5. የክፍለ ከተማና የወረዳ ጤና ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

1. የክፍለ ከተማ ጤና ጽ/ቤቶች በስራቸዉ የሚተዳደሩ የጤና ጣቢያዎች የመድሃኒት ስራ አመራሩን በተመለከተ ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ
2. በየደረጃዉ የመድሃኒት አቅርቦትና አጠቃቀሙን በተመለከተ አስፈላጊ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ያደራጃል፤ለሚመለከተው አካልም ሪፖርት ያደርጋል፡፡
3. የግብዓት አቅርቦት ስርአቱን በመከታተል የጤና ተቋማት የመድሃኒት በጀት አቅም የሚጎለብትበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
4. ለጤና ጣቢያዎች አስፈላጊውን የሰው ኃይል የማማላትና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፤
5. የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችን ጥገና በሚመለከት ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡
6. የመድኃኒት ዝውውርና ትውስቶችን በተመለከተ ክትትል ያደርጋል፡፡

## 6. የጤና ተቋማት ተግባርና ሀላፊነት

በ□ህ መመሪጸ በዝርዝር የተገለጸው የመድሃኒት አቅርቦት ስርጭትና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ተፅባራዊ ማትረፅ እአንደተጠበቀ ሆኖ ጤና ተቋማት፡-

1. የመድሀኒት አቅርቦት፣ ስርጭት፤ አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ለመከታተል ያመች ዘንድ የመደሀኒትና ሕክምና መማክርት ኮሚቴ ያቀቁማል፤ ሀላኝነቱን በአግባቡ እ□ተወ□ ስለመሆኑ የቅርብ ክትትል ያደርፋል፤
2. በተለያዩ ምክንያቶች መሰረታዊ መድሃኒቶችን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ማቅረብ አዳጋች በሚሆንበት ወቅት ወይም አቅርቦቱ የህብረተሰቡን የመግዛት አቅም ያላገናዘበ ሲሆን በወቅቱ ለበላይ አካላት ያሳውቃል፤
3. በጤና ተቋሙ □ተመ□ቡ □ስራ ሃላኝ- ችና ሰራተኞች በተለያዩ ህጋዊ መንገዶች ወ□ ተቋሙ የገቡ መድሀኒቶችን ውጤታማ በሆነ ሁኔታና ለታለመለት ዓላማ ሥራ ላይ እያዋሉ መሆናቸውን የማረጋገጥና ጥፋት ሲከሰት ወቅታዊ የማስተከከያ ዕርምጃ የመዉሰት ሀላፊነት አለበት፤
4. የተገላባጭ/ተዘዋዋሪ መድሀኒት ፈንድ አሰራርን ተግባራዊ ያደርጋል፤
5. አግባባዊነት ያለዉ የመድሀኒት አጠቃቀምን በተመለከተ ተከታታይነት ባለው መልክ ጥናት ማካሄድና በውጤቱ መሰረት የማስተከከያ □ርምጽ □ወስቴል፤
6. የመድሃኒት አገልገሎት አሰጣጡን ቀልጣፋ፤ ውጤታማ እአና ደረጃውን የጠበቀ ለማትረፅ ሀገር አቀፉ የጤና ተቋማት ደረጃ በሚያዘዉ መሰረት በቂና ለተገልጋዮች ምቹ የሆኑ የመድኃኒት ማከማቻ፣ ማዳያ፣ የምክር አገልግሎት መስጫና የመድኃኒት ቅመማ ክፍሎች በማደራጅት ተፅባራዊ ጻ□ርፉል፤ሚያስፈልገውን የመድሀኒት ባለሙያ □ሂሳብ ሰራተኛ፣ □ክለት ገንዘብ ሰብሳቢ እና ሌሎች አስፈላጊ ሰራተኞችን እንዲሟላ ያደርጋል፤
7. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 6 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሆስፒታል ለተመመላላሽ፣ ለድንገተኛ፣ ለአስተኝቶ ህክምና እና ለረጅም ጊዜ ታካሚዎች አግልገሎት የሚሰጡ ፋርማሲዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡
8. የመድኃኒት ማደያ ክፍሎች የስራ ፍሰቱን እና አገልግሎት አሰጣጡን መሰረት አድርጎ ለተገልጋዮች ምቹ በሆነ፤ ቅርበት ባለው እና በግልፅ በሚታይ ቦታ በኢትዮጵያ ሆስፒታል እና ጤና ጣቢያ አገልግሎት ትራንስፎርሜሽን ትግበራ መመሪያ መሰረት መደራጀት አለበት፡
9. ለሆስፒታሎችና ለጤና ጣቢያዎች የመድኃኒት አገልግሎት የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ፍላጎትና ምጣኔ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ባዘጋጀው የመሰረታዊ ስራ ሂደት ጥናት (ቢ.ፒ. አር) ሰነድ መሰረት መሟላት ይኖርበታል፡፡
10. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 9 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለመድኃኒት አገልግሎት የሚያስፈልገው የሰው ኃይል መጠን በየወሩ በሚዘጋጀው የአገልገሎት ሪፖርት መሰረት የ 6 ወር ግምገማ ተደርጎ በሚከተሉት የስራ ጫና ምጣኔ ስሌቶች መሰረት የሰው ኃይል

እንዲጨመር ለክፍለ ከተማ ወይም ለጤና ቢሮ ሪፖርት ማድረግ፤ በሚከተለው ዝርዝር መረጃ መሰረት ማለትም፡-

- ለተመላላሽ ህክምና የመድኃኒት አገልግሎት ለተጨማሪ 1000 ታካሚዎች ወይም 1500 የመድኃኒት የምክር አገልግሎት አንድ (1) ተጨማሪ የመድኃኒት ባለሙያ
- ለድንገተኛ ክፍል የመድኃኒት አገልግሎት ለተጨማሪ 750 ታካሚዎች አንድ (1) ተጨማሪ የመድኃኒት ባለሙያ
- ለረጅም ጊዜ ታካሚና ለተኝቶ ህክምና የመድኃኒት አገልግሎት፣ ለተጨማሪ 500 ታካሚዎች አንድ (1) ተጨማሪ ፋርማሲስት
- ለህሙማን ተኮር (ክሊኒካል ፋርማሲ) አገልግሎት ለ ሶስተኛ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃ እና አንደኛ ደረጃ ሆስፒታሎች ለሚኖሩት ተጨማሪ 25፣ 30 እና 35 አልጋዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው አንድ (1) ተጨማሪ ፋርማሲስት
- ለተጨማሪ 5000 ህሙማን አንድ (1) ተጨማሪ የፋርማሲ አካውንታንት
- በእያንዳንዱ የመድኃኒት ማደያ ክፍል አንድ (1) የእለት ገንዘብ ተቀባይ የሚያስፈለግ ሆኖ የእለት ገንዘብ ተቀባዮች በቀን በአማካኝ ከ500 ታካሚዎች በላይ የሚያስተናግዱ ከሆነ በወርሃዊ ሪፖርቱ የስራ ጫናው ታይቶ ተጨማሪ የሰው ኃይል እንዲመደብ ጥያቄ በማቅረብና በማስፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

11. ከመደበኛው የመንግስት የስራ ሰዓት ውጭ የሚመደቡት ባለሙያዎች ምደባ ቁጥርም ከላይ በ ንዑስ አንቀፅ 10 በተገለፀው መሰረት መከናወኑን ያረጋግጣል፡፡

12. በጤና ተቋማት በሚገኙት የችርቻሮ መድኃኒት ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ የመድሀኒት ባለሙያዎች በጋራ የመስራት፣ መድሀኒቶችን በጋራ የመረከብ፣ የማስተዳደር፣ የመንከባከብ እና የጋራ ሀላፊነትና ተጠያቂነት ያለባቸው መሆኑን በሰነድ እንዲረጋገጥ እና በዚሁ መሰረት የጋራ ተጠያቂነት ተግባራዊ እንዲደረግ ያደርጋል፡፡

13. እያንዳንዱ የመድኃኒት ባለሙያ በግልም ሆነ በጋራ ለሚከሰት ብክነት ወይም ጉድለት ባለሙያው ወይም የባለሙያው ዋስ/ተያዥ ተጠያቂነት ያለበት አሰራር መኖሩን ይቆጣጠራል፡፡

14. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 12 እና 13 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሙያዎች በጋራ ተጠያቂ የሚሆኑት በስራ ባህሪው አስገዳጅነት በጋራ ለሚከናወኑ ስራዎች ማለትም የመድኃኒት ፍጆታ ሪፖረት ማድረጊያ፣ መጠየቂያና መቀበያ ፎርም መሙላት ፤ መድኃኒት ከመጋዘን ፈርሞ ማውጣት፤ መድኃኒት ማደል ፤ ቢን ካርድ መሙላት፤ መድኃኒት መቁጠር፤ የሽያጭ መረጃ መያዝና መሰነድ፤ የመድኃኒት አጠቃቀም ግምገማ መስራት፤ በአጠቃላይ መድኃኒቶችን የማደል፤ የማስተዳደር፤ የመንከባከብ፤ እንቅስቃሴያቸውን የመከታተልና የመቆጣጠር ስራዎችን ይፈፅማል፡፡ ይሆናል፡፡

15. የመድሃኒት አቅርቦት □እና ስርጭት □እንዲሁም የአገልፅሎት አሰ□ጡን በሚመለከት በዉስዓ ኦቲተር በ□ሩብ □መቱ □እና በው□ ኦቲተር ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ኦዲት ያስደርጋሉ፡፡ የኦዲት ሪፖርቱ ለተቋሙ ከፍተኛ አመራር ወይም ቦርድ በማቅረብ ተቪዉ □እርምጃ □እአንዲወሰድ ያደርጋሉ፡፡

16. የመድሀኒት አቅርቦትና ስርጭት ሂደትን በተመለከተ በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር □ሊሲ- ች፤ ህጎችና መርሆ- ች መሰረት ያከናዉናሉ፡፡

17. የመድሃኒት አቅርቦት፤ ስርጭትና አጠቃቀም መረጃ አያያዝ ስርዓት ግልጽና ለኦዲት ምቹ እንዲሆን ማድረግ አለባቸው፡፡

18. በእርዳታ የሚያገኛቸው መድሃኒቶች ከህጋዊ ምንጭ መሆናቸውን ማረጋገጥና ከለጋሹ አካል የመድሃኒቱን ዝርዝር መረጃ የያዘ ሰነድ መቀበል አለባቸው፡፡

19. ህጋዊ ካልሆኑ ምንጮች መድሃኒት ሲቀርብለት ወዲያውኑ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ወይም የፍትህ አካል የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

20. ለተለያዩ አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ወጪ የተደረገ፣ ጥቅም ላይ የዋለ እና

ያልዋለ መድሃኒት ክትትል የሚደረግበትና ለህገወጥ መድኃኒት ዝውውር ክፍተት የማይፈጥር የአሰራር ስርዓት መቅረጽና ተግበራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡

21. በጤና ተቋማት መካከል የሚደረግ የመድሃኒት ዝውውር ወይም ልውውጥ ግልጽነትና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ መልኩ በዚሁ መመሪያ በተገለፀው ዝርዝር የአሰራር ስርዓት መሰረት መሆን አለበት፡፡

22. ማንኛውም ጤና ተቋም የህክምና መሳሪያዎችን አስተዳደር የሚከተታል የህክምና መሳሪያዎች መማክርት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የተለያዩ የስራ ክፍሎች የተውጣጡ ባለሙያዎች የተካተቱበት ሊኖረው ይገባል፡፡

23. ማንኛውም ጤና ተቋም በሚሰጡት ጤና አገልግሎትና የወደፊት የጤና አገልግሎን የማስፋፋት እቅድ መሰረት ባደረገ መልኩ ቋሚ የህክምና መሳሪያዎች መለዋወጫና የሚጠቀሙትን ሪአጀንቶችን እንዲሁም ጥገናን መሰረት ባደረገ መልኩ የግዥ እቅድ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

24. ጤና ተቋማት በራሳቸው አቅም መጠገን ያለባቸውን የህክምና መሳሪያዎች መጠገንና፤ ከተቋሙ ውጭ ለሚጠገኑት ህጋዊ ከሆነ አካል ጋር የክብካቤ ውል በመግባት ማስጠገን አለባቸው፡

25. ቋሚ የህክምና መሳሪያዎች በመንግስት ቋሚ የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት መተዳደር ይኖርባቸዋል፡፡

26. ማንኛውም ጤና ተቋም የህክምና መሳሪያዎችን በትክክልና በጥንቃቄ ለመጠቀም ቅደም ተከተሉን የጠበቀ የአሰራርና የአጠቃቀም ስርአት አዘጋጅተው በእያንዳንዱ መሳሪያ ላይ መለጠፍ ይኖርበታል፡፡

27. ለጤና ተቋማት የህክምና መሳሪያዎችን በግዢም ሆነ በእርዳታ ሲቀርቡ እንዳስፈላጊነቱ በህክምና መሳሪያው አቅራቢ ድርጅት ለባለሙያዎች አስፈላጊው ስልጠና መሰጠቱን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

28. የህክምና መሳሪያዎች በእርዳታ ወደ ተቋሙ ሲገቡ ስልጣን የተሰጠው አካል ባወጣው መመሪያ መረት መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

29. የህክምና መገልገያ መሳሪዎች አያያዝና አጠቃቀም በኢትዮጵያ ሆስፒታል እና ጤና ጣቢያ አገልግሎት ትራንስፎርሜሽን ትግበራ መመሪያ መሰረት መደራጀት አለባቸው፡

30. ማንኛውም ጤና ተቋም አዲስ የህክምና መሳሪያዎችን ከማስገባቱ በፊት ለህክምና መሳሪያው በደረጃው መሰረት የሚያስፈልገው ቦታ፤ የኤልክትሪክና የውሃ መስመሮች እንዲሁም ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

31. የተገዙ ወይም በእርዳታ የመጡ የህክምና መሳሪያዎች ተቋሙ ከመረከቡ በፊት የሚሰሩ መሆናቸው፤ በቂ የሆነ ማንዋል እና መለዋወጫ እቃ፤ የደህንነት መስፈርቶች የሚያሟላና በተጠየቀው መስፈርት መሰረት የመጣ መሆኑን በባለሙያ መረፋቶዒ ይሮርባቸዋል፡፡

32. የጤና ተቆሙ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች ሲሰበሩ፤ሲጠፋ፤ሲበላሹ በጤና ላይ ጉዳት ሲያደርሱ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀው ቅጽ መሰረት ተመዝግቦ ሪፖረት መደረግ አለበት፡፡

33. የህክምና መሳሪያዎችን በህክምና መሳሪያዎች ክምችና የአገልግሎት መስጫ ክፍል ውስጥ ያሉትን የህክምና መሳሪያዎች በህክመና መሳሪያዎች ቆጠራ ቅጽ መሰረት መደረግ ይኖርበታል፡፡

34. ከአገልግሎት ውጭ የሆኑና ተጠግኖ ጥቅም ላይ የማይውሉ የሕክምና መሳሪያዎች ወደፊት የኢፌዲሪ የምግብ፣ መድሐኒት እንክብካቤ በሚያወጣው የሕክምና መሳሪያዎች ጥቅም ላይ የማይውሉ የህክምና መሳሪያዎች አወጋገድ መመሪያ መሰረት መሆን ይኖርበታል፡፡

35. በማህበረሰብ ጤና ክብከቤ አሀድ ቡድን በማህበረሰብ ደረጃ አገልግሎት ላይ የሚውሉ መድሀኒቶችንና የህክምና መገልገያ መሳሪያ- ችን ዉ□ተማ በሆነ ሁኔተ□አና ለተለመለት

□ላማ ብቻ ስራ ላ□ መኘላቸውን ጸረፉፅ□ል □አንደ አንድ □አ□ላ □አል ፅብአቶችን ጸቀርባል ይከተተላል □ቆ□□ራል።

## 7. የመድሀኒት አጠቃቀምና አገልግሎት አሰጣጥ ሥነ-ምግባር

የጤና ባለሙያዎችን የስራ ስነ ምግባር በተመለከተ በሌሎች ህጎች እና ደንቦች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነዉ ይህንን መመሪያ ዉ□ታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ ይቻል ዘንድ በመድሀኒት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተሰማሩ ባለሞያዎች የሚከተሉት የሥነ-ምግባር መርሆዎችን ተከትለው ተግባራቸውን ማከናወን አለባቸው፡፡

1. የተፈጠረ ወይም ሊፈጠር የሚችል የጥቅም ግጭትን ለበላይ ማሳወቅና ራስን ከሂደቱ ማግለል፣
2. ከመድሀኒት ግዥ ጋር በተያያዘ ስጦታ ወ□ም □ስራ ዕድል ወይም የገንዘብ ዋጋ ያለው ነገር ወይም ሌላ አይነት አገልግሎት አለመቀበል፡፡
3. በስራ ሂደት ያወቋቸውን፣ ሊ□ጸሙ □ታሰቡ ወይንም የተፈጸሙ የሙስና ተግባራትን ለህግ አስፈፃሚ አከላት የማሳወቅና ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋት የሚደረገውን ጥረት ማገዝ፡፡
4. ከአገልገሎቱ ጋር በተያያዘ ለሚገኙ ማንኛዉም መትሃኒቶች ተቆርቋሪ መሆን፡፡
5. በመድሀኒት አግልገሎት አሰጣጥ ሂደት ላይ አድልዎ አለማድረግ፡፡
6. የተሰጣቸውን ሀላፊነት የአገልጋይነት መንፈስ በመያዝና በቁርጠኝነት መወጣት፡፡
7. የተጠቃሚውን ምስጢር መ□በቅ፣ ለህሙማን የታዘዙትን መድኃኒቶች ወይም ያዘዘዉን ባለሙያ በተገልጋዩ ፊት አለማጣጣል፡፡
8. የመድሃኒት አገልገሎት አሰጣጥ ሥርጭትና አጠቃቀምን በተመለከተ ሙያው የሚጠይቀውን ሰነምግባር ማክበር፡፡
9. ለመድኃኒት አገልግሎት ተጠቃሚዎች በሙሉ ርህራሄ እና ቅንነት የተሞላበት አገልግሎት መስጠት፤
10. ሙያው የሚፈልገውን የላቀ እውቀትና ክህሎት በመጠቀም ከስራ ባልደረቦቹ፤ ከታካሚዎች እና ከታካሚ ቤተሰቦች ጋር ጠንማ የሆነ ግንኙነት መፍጠር፤
11. በተሰማሩበት ሞያ ክብር እና ሞገስ የሚሰማቸው እና ህዝብ እና ሃገርን በማገልገላቸው እርካታ የሚያገኙና የሚደሰቱ መሆን፤
12. ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራርን ተግባራዊ በማድረግ ለሌሎች አርዓያ መሆን፤
13. የህብረተሰቡን ባህል፤ ሐይማኖት፣ ቋንቋ፣ ወግና ልማድ ማክበርና እና ስራቸው ከአድልዎ በፀዳ መልኩ መተግበር
14. ለሙያ ስነ-ምግባር ተገዥ የሆኑ፤ የሙያ አጋራቸውን የሚያከብሩ እና የማንግስትን የስራ ሰዓት ሳይሸራርፉ ስራቸውን በወቅቱና በጥራት ማከናወን፤
15. ሱስ የሚያስዙ መድሃኒቶችን ለራሱ፣ለሙያ ባልደረባወም ሆነ ለተገልጋይ ያለአግባብ የሚጠቀሙ እና የሚይሰጡ፤
16. ለተገልጋዮች ተገቢውን የመድኃኒት አጠቃቀም ገለፃ፣ መረጃ እንዲሁም የምክር እና ድጋፍ አገልግሎት መስጠት፤
17. ከአገልግሎቱ ጋር በተያያዘ ለሚገኙ ማንኛወም መድኃኒቶች ተቆርቋሪ መሆን፤
18. የተጠቃሚውን ምስጢር ማጠበቅ፣ ለህሙማን የታዘዙትን መድኃኒቶች ወይም ያዘዘውን ባለሙያ በተገልጋዩ ፊት አለማጣጣል፡፡

# ክፍል ሶስት

## የመድሃኒት አቅርቦት፣ ክምችት፣ አያያዝ፣ ስርጭት፣ ሽያጭ እና አወጋገድ ስርዓት

## 8. የመድሀኒት አቅርቦት

*ማንኛውም ጤና ተቋም፡-*

1. የአካባቢውን የበሽታ ስርጭት፤ የጤና ተቋሙን አይነትና ደረጃ፤ አገር አቀፉን የመድሃኒት ዘርዝር እና ሌሎች መመዘኛዎችን መሰረት በማድረግ ቢያንስ በአመት አንዴ የሚከለስ ለተቋሙ የሚያስፈልጉ መድሃኒቶችን ዝርዝር ለጤና አገልግሎቱ ካላቸው ተፈላጊነት አንጻር ቅደም ተከተል በማስጠት በመድሃኒትና ህክምና መማክርት አማካይነት ማዘጋጀት አለበት፡፡
2. የመድሃኒት ማዘርዘራቸውን በአዲሱ በጀት አመት እስከ ሀምሌ 30 ድረስ መድሃኒት ማዘርዝሩ ላይ አዲስ የሚጨመሩ ካሉ በማከተት ወይም ከመዘርዝሩ የሚወጡ ካሉ በማስወጣት ለግዢ ዝግጁ ማድረግ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ጤና ተቋም ለሚቀጥለው የበጀት አመት አዳዲስ የሚከፈቱ አገልግሎቶችን መሰረት ያደረገና፣ የተቋሙን የበጀት መጠን ያገናዘበ የመድሃኒት ትመና በማድረግ ጥቅምት 30 ድረስ ሚጀውን በተዘጋጀው ቅፅ ላይ አጠናቅሮ ለመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ፣ለቢሮው እና ለሚመለከታቸው አካላት ማድረስ ይኖርበታል፡፡
4. የመድሃኒት ትመናው የሚከናወነው በተቀናጀ የመድሀኒት ሚጃ አያያዝ ስርዓት ማለትም የመድሀኒት ፍላጎቱ ከዚህ በፊት የነበረውን የመድሃኒት ፍጆታ የሚጠውን የህክምና አገልግሎት እና የአገልግሎት ማስፋፋትን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡
5. ከላይ በንዑስ 1 እና 2 የተጠቀሰው የመድሃኒት ሚጣና ትመና እንደተጠበቀ ሆኖ የግዢ ወሳኔው ነፍስ አድን የሆኑትን መድሀኒቶች ቅድሚያ የሰጠ፣ ካለው የመድሀኒት በጀት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን (ABC analysis and ABC/VEN reconciliation) በማድረግ የግዥ ጥያቄውን በወቅቱ ማቅረብ ይኖርበታል፤
6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ጤና ተቋም የመድሃት ግዢ እቅድ ሲያዘጋጅ በመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ አዋጅ ቁጥር 553/99 እና በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የግዥ መመሪያ መሰረት መሆን ይኖርበታል፡፡
7. የሚያስፈልጋቸውን የመድሃኒት አይነትና መጠን ከወሰኑ በኋላ በየሁለት ወሩ ከመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ ለአራት ወራት ያህል የሚያገለግላቸውን የመድሃኒት ፍጆታ የግዢ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
8. የማንኛውም መድኃኒት የፍጆታው መጠን ከ15 ቀን በታች ከመሆኑ በፊት  አስፈላጊውን የመጠን ትመና በማድረግ ከመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ መግዛት ይኖርበታል
9. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 6 እና 7 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ መድሃኒቶቹ አለመኖራቸው ሚረጋገጫ ሲሰጥ ጤና ተቋሙ በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የግዢ መመሪያ መሰረት ከሌላ አቅራቢ ድርጅት የመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሴ የሚያቀርብበትን ጊዜ ታሳቢ በማድረግ በአንድ ጊዜ ግዢ ቢበዛ ለስድስት ወራት የሚያገለግል መድሃኒት መጠን መግዛት ይኖርበታል፡፡
10. የመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ ለሚያቀርባቸው መድሃኒቶች ጤና ተቋሙ በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የግዢ መመሪያ መሰረት ከሌላ አቅራቢ ድርጅት የበጀት አመቱን እቅድና  ፍላጎት ባገናዘበ ሜኩ መግዛት ይኖርበታል፡፡
11. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 8 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ መድሃኒት በተቋሙ ግዢ በሚፈጸምበት ወቅት በጨረታ ቡድኑና በቴክኒክ ኮሚቴ ወስጥ የፋርማሲና የህክምና መሳሪያዎች ባለሙያ ሙያዊ እገዛ ለማስጠት አባል ሆነው ማሰራት አለባቸው፡
12. እንደ ጤና ተቋሙ ነባራዊ ሁኔታ ከመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ ለሚገዙ ግዢዎች የመድሃኒት ባለሙያ እና ግዢ ኦፊሰሩ ጋር ተረክቦ ለተቋሙገቢ ያደርጋል፡፡

13. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 12 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የህክምና መሳሪያዎች ግዥ ሲፈፀም፣ የህክምና መሳሪያ ባለሙያው ወይም የመሳሪያው ተጠቃሚ እገዛ ሊኖረው ይገባል፡፡

14. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 11፣ 12 እና 13 የተጠቀሱት እንደተጠበቀ ሆኖ የመድኃኒት ባለሙያው አስፈላጊውን መረጃ በማጠናቀር ለተቋሙ ክፍያና ፋይናንስ በወቅቱ የግዢ ሰነዶችን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

15. በተቀናጀ የመድሀኒት መረጃ አያያዝ ስርዓት ማስረት የጤና ተቀማት የመድሃኒት አቅርቦት ፍላጎታቸውን በመድሃኒት ሪፖርት ማድረጊያና ማጠየቂያ ቅጽ(RRF) ማስረት ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

16. በግዥም ሆነ በእርዳታ የቀረበለት መድሃኒቶች የተቋሙን ፍላጎት ማስረት ያደረገና የመድሃኒቶችን ህጋዊነት በሚያረጋግጡ ሰነዶች የተፈጸመ መሆኑን ሚረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

17. የመድሃኒት አቅርቦትና ክምችት አስተዳደር በመድሃኒት ባለሙያ እንዲመራ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 9. መድኃኒቶችን ገቢ ስለማድረግ

1. ማንኛውም በግዥ የቀረበ መድሀኒት ወደ መድሀኒት መጋዘን ወስጥ ከማባቱ በፊት የተጠየቀው አይነትና ማጠን መሆኑን፣ ያልተበላሸ እና የአገልግሎት ጊዜው ያላለፈ መሆኑንና የተሟላ የመድሃኒት ማገለጫ (labeling) ያለው መሆኑን ማምግምና ሚረጋገጥ አለበት፤
2. ማንኛውም በእርዳታ የተገኘ መድሀኒት ወደ መድሀኒት መጋዘን ወስጥ ከማባቱ በፊት ያልተበላሸ እና የአገልግሎት ጊዜው ያላለፈ መሆኑንና የተሟላ የመድሃኒት ማገለጫ (labeling) ያለው መሆኑን ማምግምና ሚረጋገጥ አለበት፤
3. መድሃኒቶች በስራ መመሪያው መሰረት መጓጓዝ ያለባቸው ሲሆን ከቁጥጥር ውጭ በሆነ ሁኔታ መድሃኒቶች በመጓጓዙበት ወቅት ለሚደርስባቸው እንከን ለዚሁ አገልግሎት በተዘጋጀው መመዝገቢያ ቅጽ መሰረት ተመዝግበው ለጤና ተቋሙ ሪፖርት መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ማንኛውም መድኃኒት ወደ ህክምና ተቋሙ ገቢ ሲደረግ ለዚሁ አላማ ተብሎ በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በሚታተም የመድኃኒት የገቢ ደረሰኝ (ሞዴለ 19/ጤ) መሰረት ሚጃዎች ተሞልተዉና በየበጀት ምንጫቸው በመደበኛ በጀት፣ በእርዳታ እና ቋሚ የህክምና መሳሪያዎች በሚል ተለይተዉ መሆን አለበት፡፡
5. የመድሃኒቶችን የገቢ ደረሰኝ የሚሰራለቸው የመድሃኒቶችን አቅርቦትና ስርጭት መከታተያ ኤሌክትሮኒክስ የሚጃ አያያዝ ስርአት አማካኝነት መሆን ይኖርበታል፡፡
6. መድሃኒቶች ወደ ጤና ተቋሙ ገቢ በሚደረግበት ወቅት እንደአስፈላጊነቱ የተቋሙ የበላይ ሃላፊ የተገዛው መድሃኒት በተገቢው ሜኩ መግባታቸውን የሚያረጋግጥ ባለሙያ በመመደብ ሊያረጋግጥ ይችላል፡፡
7. በጤና ተቋማት የመድሃኒት ክምችትና የመድሃኒት አቅርቦትና ስርጭትን መከታተያ ኤሌክትሮኒክስ የሚጃ አያያዝ ስርአት የሚከናወኑት በተለያየ የመድሃኒት ባለሙያ ሲሆን የመድሃኒት ክምችት ባለሙያው የገቢ ደረሠኞቹን ትክለኝነት በሚረጋገጥ ፈርሞ መድሃኒቶችን ገቢ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
8. ማንኛውም ጤና ተቋም መድሀኒት ገቢ ያደረገበትን የገቢ ደረሰኝ ቅጅ የተቋሙን ማህተም በማድረግ ለአስረካቢው አካል እና ሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት መስጠት አለበት፤
9. ማንኛውም ገቢ የሚደረግ መድኃኒት በመጠየት ሰነድ ላይ ዋጋው ያልተገለጸ ከሆነ በዋጋ ገማች ኮሚቴ ዋጋው ተገምቶና በተቋሙ የበላይ ሃላፊ ጸድቆ በገቢ ሰነድ ላይ ዋጋው ተተክሎ ከቀሪ የገቢ ደረሰኙ ጋር ተያይዞ መቀመጥ ይኖርበታል፤
10. ማንኛውም የጤና ተቋም የመድሃኒት ግዥና ክምችት አስተዳደር በተለያዩ የመድሃኒት ባለሙያዎች መከናወናቸውን ያለባቸው ሲሆን መድሃኒት ወጪ የሚደረገው ደግሞ በተፈቀደለት የተቋሙ የጤና ባለሙያ መሆኑን ሚረጋገጥ አለበት፡፡
11. መድሃኒት ገቢና ወጪ ሲደረግ አንድ ኮፒ የገቢና ወጪ ደረሰኝ ለሰቶክ ካርድ ጸሃፊ እንዲደርሰው በማድርግ ሚጃዎቹ በወቅቱ መያዝ አለባቸው፡፡

## 10. የመድኃኒት ክምችትና አያያዝ

1. ማንኛውም የጤና ተቋም ገቢ ያደረጋቸውን መድኒቶች የመድሃኒት፣ ምግብ እና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ባወጣው የመድሃኒት መጋዘን ደረጃ መሰረት በተገቢው ስርዓት ተደርድረው መቀመጣቸውን ሚረጋገጥ አለበት፡፡
2. አዳዲስ መድሃኒቶች በግዝም ሆነ በእርደታ ወደ ጤና ተቋሙ ሲገቡ የመድሃኒት አቅርቦት ባለሙያ ከመድሃኒት ሚጃ ባለሙያ ጋር በመተባበር ለመድሃኒት ሚዲያ ክፍሎችና መድሃኒት ለሚያዝዙ የጤና ባለሙያዎች (Prescribers) በወቅቱ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
3. የመድሀኒት መጋዘን እና የመድኃኒት ችርቻሮ ክፍሎች ማለያየትና በተለያዩ የመድሃኒት ባለሙያዎች መተዳደር አለባቸው፤
4. ማንኛውም ጤና ተቋም አግባብ ባለው ደረጃ እና የአምራቾች ማስፈርት መሰረት መድሀኒቶችን እንደባህሪያቸው እና እንደየበጀት ምንጫቸው ተለይተው በተገቢው ቦታ፣ የሙቀት ማጠን፣ ጊዜ፣ የጸሀይ ጨረር፣ ንጽህና እና ሌሎች ተገቢ የሆኑ ጥንቃቄዎችን በማሟላት ማያዙን ሚረጋገጥ አለበት፤
5. ጤና ተቋማት መጋዘናቸውን የመድሃኒት፣ የሰፕላይ እና የህክምና መሳሪያ (Medicine, Supplies and medical equipment) ብለው በተለያየ ክፍልና ባለሙያ እንዲተዳደር ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

6. ማንኛውም የመድሃኒት ባለሙያ የማጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን እና በልዩ ልዩ ምክንያት አገልግሎት ለሰጡ የማይችሉ መድሀኒቶችን፣ አገልግሎት ከሚሰጡ መድኒቶች ለይቶ ማስቀመጥና በወቅቱ ሪፖርት ማድረግ አለበት፤
7. ማንኛውም ጤና ተቋም ተቀጣጣይነት ያላቸውን ወይም ሌሎች መድሀኒቶችን ሊበክሉ የሚቹሉ ኬሚክሎችን፣ የህክምና መሳሪያዎችን እና ማልገያዎችን ከሌሎች መድኃኒቶች ለይቶ ማስቀመጥ አለበት፤
8. ማንኛውም የመድኃኒት ባለሙያ የሚዘቸውን መድሀኒቶች የጠቀሜታ ጊዜያቸውን ቅደም ተከተል ማስረት በማድረግ የአገልግሎት ጊዜ የሚያልፍባቸውን ቀድሞ ማውጣት ወይም ጥቅም ላይ ማዋል አለበት፤፡
9. ማንኛውም ጤና ተቋም የመድሀኒት ክምችት እና እንቅስቃሴን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ቢን ካርድ እና ዘመናዊ ኤሌክትሮኒክስ የሚጃ አያያዝ ስርአት እንዲሁም ሌሎች ማገዶችን በማጠቀም በአግባቡ እና በወቅቱ መመዝገባቸውን መከታተል አለበት፤፡
10. ማንኛውም ጤና ተቋም በማዘርዝሩ ያካተታቸውን መድሃኒቶች ባልተቆራረጠ ሁኔታ ለህብረተሰቡ እንዲደርሱና እንዳይባክኑ ወቅታዊ የፍጆታ መዋዠቅን እና የማጠቀሚያ ጊዜን ባገናዘበ መልኩ ክምችቱ ያለበትን ደረጃ ማምገምና ለችግሩ መፍትሄ መስጠት አለበት፤
11. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 10 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመድሃኒት ክምችት ባለሙያው፣ የመድሃኒት አቅርቦት ባለሙያ፡ የመድሃኒት ክምችትና ስርጭት ኤሌክትሮኒክስ የሚጃ አያያዝ ስርአት ባለሙያ እና የመድሃኒት አቅርቦት፣ ክምችትና ስርጭት ቡድን መሪ በየወሩ የመድሃኒት ወቅታዊ የፍጆታ መዋዠቅን እና የማጠቀሚያ ጊዜን ባገናዘበ መልኩ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ ሚጃዎችን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
12. ማንኛውም የጤና ተቋም ልዩ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸውን መድሀኒቶች ማለትም፦ - ናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒቶች፣ መርዞችን፣ በየወሩ ክትትል በማድረግ ወጠቁን ለሚመለከተው አካል ማቅርብ ይሮርበታል፡፡
13. ማንኛውም የጤና ተቋም ቀዝቃዛ ሰንሰለት የሚፈልጉትን መድሀኒቶች በየእለቱ በ12 ሰአት ልዩነት የቅዝቀዜው ማጠን መመዝገብ ይኖርበታል፡፡
14. ማንኛውም በግዥ ወይም በእርዳታ የተገኘ መድሀኒት የምርት እንከን ያለበት ሆኖ ሲገኝ በሌላ ቦታ የተሰራጨው የህብረተሰብን ጤና እንዳይጎዳ እርምጃ ይወሰድበት ዘንድ ለመድሃኒት፣ ምግብና ጤና ክብካቤና አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣንና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ማድረግ አለበት፤
15. በሆስፒታሎች የመድሃኒት ክምችት ባለሙያ፣ የስቶክ ካርድ ፀሃፊና የመድሃኒት ክምችትና ስርጭት መቆጣጠሪያ ኤሌክትሮኒክስ የሚጃ አያያዝ ስርአት ባለሙያ በየአስራ አምት ቀኑ ወቅታዊ የሆነ የሚጃ ልወውጥ በማድረግ የሚጃ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመድሃኒት አቅርቦት ባለሙያ ሪፖርት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
16. የመድሃኒት አቅርቦት ባለሙያ ከመድሃኒት ክምችት ባለሙያ ጋር በመሆን ወቅታዊ የሆነ የመድሃኒት አቅርቦት እንዲኖር የመድሃኒት ክምችት ማጠንን በመተንተት (stock status analysis) የመድሃኒት የግዥ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 11.የመድሃኒት ስርጭት

1. ከጤና ተቋሙ የመድሃኒት ማጋዘን ለተለያዩ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ወጪ የሚደረጉ መድሃኒቶች ክፍሎቹ ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ፤ ከጤና ተቋሙ የመድሃኒት ማዘርዝር የተወሰደ፤ የመድሃኒትና ህክምና መመክርት ለየክፍሎቹ በሚያዘጋጀው ማዘርዝር ማስረት መሆን አለበት፤
2. የጤና ተቋሙ የተለያዩ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች የመድሃኒት ማጠይቅ ሲያቀርቡ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው የወስጣዊ መድሃኒት ሪፖረት ማድረጊያና ማጠየቂያ ቅጽ (Internal Facility Reporte and Resupply Form (IFRR)) ላይ አስፈላጊ ሚጃዎችን በመሟላት መሆን ይኖርበታል፤
3. የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ በሚከልበት ወቅት የትርፍ ጣሪያው በ 20% የሚሰብ ሆኖ ነገር ግን ቅንጣት ዋጋው መሉ ሳንቲምና የአምስት ሳንቲም ብዜት ካልሆነ የማጠጋጋት ስራው ሁሌም ወደ ላይ ይሆናል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመድሃኒት የመሸጫ ዋጋ የማህበረሰቡን የመግዛት አቅም ያገናዘበ፣የበሽታ ዓይነት መሆኑን በማየት የትርፍ ጣሪያው ከ 20% ያነሰ ወይም ያለ ትርፍ መሸጥ ሲኖርበት(በመጠበት ዋጋ ) በተቋሙ ሜጅመንት ተወስኖና በተቋሙ የበላይ ሀላፊ ፀድቆ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

5. በንዑስ አንቀጽ 3 በተገለፀው መሰረት የመሸጫ ዋጋ ለማስላት በሚደረግ የማጣጋጋት ሂደት ጠቅላላ የመሸጫ ዋጋው ከተወሰነው የትርፍ ጣሪያ በላይ ሆኖ ቢገኝ ተጠያቂነትን አያስከትልም ፡፡

6. የጤና ተቋሙ የመድሃኒት መጋዘን ክፍል ባለሙያ የአገልግሎት ክፍሎች በወጣላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የመድሀኒት ጥያቄ በቅጹ መሰረት ተሞልቶ እና በፋርማሲ ክፍል ኃላፊ ተፈቅዶ ሲቀርብለት በቀረበው መረጃ መሰረት ፍጆታቸውን በማስላት በመጀመሪያ የመድሃኒት ክምችትና ስርጭት መቆጣጠሪያ ኤሌክትሮኒክስ የመረጃ አያያዝ ስርአት መረጃውን በማስገባት በማገኘው መረጃ መሰረት የሚያስፈልገውን ማጠን በመድኃኒት ወጭ ደረሰኝ (ሞዴል 22/ጤ) ወጪ ማድረግ አለበት፤

7. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ጤና ተቋማት የመድሃኒት ክምችትና ስርጭት መቆጣጠሪያ ኤሌክትሮኒክስ የመረጃ አያያዝ ስርአት ባለሙያ የአገልግሎት ክፍሎች በወጣላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የመድሀኒት ጥያቄ በቅጹ መሰረት ተሞልቶ እና በፋርማሲ ክፍል ኃላፊ ተፈቅዶ ሲቀርብለት በቀረበው መረጃ መሰረት በመጀመሪያ በ ኤሌክትሮኒክስ የመረጃ አያያዝ ስርአት መረጃውን በማስገባት በማገኘው መረጃ መሰረት የሚያስፈልገውን ማጠን የመድኃኒት ወጭ ደረሰኝ በማዘጋጀት ለመድሃኒት ክምችት ባለሙያ ማስጠት አለበት፤

8. የመድሃኒት ገቢና ወጪ የተሰራባቸዉ ቅጂ ሰነዶች በክምችት ተቆጣጣሪ ሰራተኛ ፋይል መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

9. መድሃኒት የተጠየቀባቸው እና ወጪ የተደረገባቸው ሰነዶች በመድሃኒት መጋዘን ሃላፊና በአገልግሎት ክፍሎች በአግባቡ ፋይል ተደርገው መያዝ አለባቸው፤

10. ማንኛውም መድሀኒት ከመጋዘን ወጭ በሚደረግበት ጊዜ አሰራሩ የማጠቀሚያ ጊዜያቸው ቀድሞ የሚያበቁትን መድኒቶች ቅድሚያ በማስጠት መርህ ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል፡፡

11. ማንኛውም መድሃኒት ከመጋዘን ወጪ ሲሆን፣ ወደ መጋዘን ገቢ ሲደረግ፤ የማጠቀሚያ ጊዜው አልፎ፤ ጉዳት ደርሶበት ወይም የምርት እንከን ተገኝቶበት ከክምችት ሲለይ እንዲሁም በቆጠራ ጊዜ ወዲያውኑ በክምችት መከታተያ ካርዶች ላይ መመዝገብ አለበት፡፡

**12. መድሃኒትን ከአንድ ጤና ተቋም ወደ ሌላ ጤና ተቋም መድሃኒትን አዘዋወሮ ስለማጠቀም የመድሀኒት ዝውውር ቅድመ ሁኔታዎች፡ -**

1. ማንኛውም ጤና ተቋም መድሃኒቶችን ማዘዋወር የሚችለው የተቋሙን የመድሃኒት የመያዝ ደረጃ ባገናዘበ መልኩ ብቻ መሆን አለበት፡፡
2. የመድኃኒቶቹ የክምችት ማጠን በመድሃኒቱ የህልፈት ጊዜ ወስጥ ተጠቅሞ ሚጨረስ እንደሚይቻል በመድሃኒትና ፈወስ መማክርት ኮሚቴ ሲረጋገጥ፤
3. መድኃኒቶቹ በጤና ተቋሙ የሚያስፈልጉ መሆናቸው ወይም በተለያየ ምክንያት ማጠቀም የሚይቻልበት ሁኔታ መኖሩን በመድሃኒትና ህክምና መማክርት ሲረጋገጥ፤
4. በሌላ ተቋም የመድኃኒቶች እጥረት ተከስቶ በተቋሙ መድሃኒቱ ለጠየቂው ተቋም ቢሰጥ የመድሃኒት እጥርት በሰጪው ተቋም እንደሚይከሰት በሚረጋገጥ የመድሃኒት ዝውውሩን ሊፈቅድ ይችላል
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በተቋማት ስምምነት መሰረት በሁለቱ ተቋማት በጋራ መግባባት መሰረት ይከናወናል፡፡
6. ጤና ተቋማት የመድሃኒት እጥረት ገጥሟቸው የሚጠይቁትን መድሃኒት ባለው የህልፈት ጊዜ ወስጥ ተጠቅመው የሚጨርሱት (Months of Stock) መሆኑን ሚረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡
7. በሁለት ጤና ተቋማት መካከል ያለው የመድሃኒት ዝውውር ምክንያት መረጃ ዝውውሩ ከሚቀዱ በፊት መረጃው በጤና ተቋማቱ ሃላፊዎች ቀርቦ ማምግም ይኖርበታል፡፡
8. ቢሮው በከተማ አስተዳደሩ ለተለያዩ የድንገተኛ አገልግሎቶች ለሚያቋቁመው ጊዜያዊ የጤና አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የሚውል መድሃኒት የጤና ተቋማትን ሲጠይቅ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ ይኖርበታል የተቋሙን ነባራዊ ሁኔታ በገናዘበ መልክ መሆን አለበት፡፡
9. የመድሃኒት ዝውውሩን የጠየቀው ጤና ተቋም በሌላ ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ሰር የሚተዳደር ከሆነ ስምምነቱ በሁለቱ ጤና ቢሮዎች መካከል ይሆናል፡፡

10. የግል ጤና ተቋማት የመድሃኒት እጥረት አጋጥሟቸው የመድሃኒት ዝውውሩ ከጠየቁ ዝውውሩ የሚፈቀደው ጥያቄያቸው ያለክፍያ ለሚሰጡ የህክምና አገልግሎቶች (ለሳንባ ነቀርሳ፣ የኤችአይቪ፤ ለእናቶችና ህፃናት አገልግሎት የሚውል ክትባት) የሚውል መድሃኒት ሲሆን ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡

11. የመድሃኒት ዝውውሩ ተግባራዊተነት በከተማ አስተዳደሩ ከሚተዳደሩ ጤና ተቋማት በተጨማሪ በከተማ አሰተዳደሩ የሚገኙ የመንግስት ፌደራልና ሚኒስቴሪያ ሆስፒታሎችን ይጨምራል

## 13. መድህኒትን ስለማዘዋወር

1. ማንኛወም ጤና ተቋም ከሌላ ጤና ተቋም የመድሃኒት ዝውውር ሲጠይቅ የጤና ተቋሙ የበላይ ኃላፊ የመድሃኒት ባለሙያን በመወከል ህገዊ የተቋሙ ማህተም ያረፈበት፤ የሚፈለጉ መድሃኒቶችን ዝርዝርና ማጠን የያዘ ደብዳቤ አስይዞ መላክ ይኖርበታል፡፡
2. የመድሃኒት ማከማቻ ክፍሉ የተጠየቁትን መድሃኒቶች ወጪ ከማድረጉ በፊት በሰጪው ጤና ተቋሙ የበላይ ኃላፊ መፈቀዱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
3. የወጪ ሰነዶች ኮፒና ሌሎች መረጃዎች በተገቢው መልኩ ተዘጋጅተው ለሚመለከታቸው አካላት መድረስ ይኖርባቸዋል፡፡
4. መድሃኒቶች የገቢ ስርአት በተከተለ መልኩ ተቀባዩ ጤና ተቋም መድሃኒቶችን ገቢ በማድረግ አንድ ኮፒ ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር እስከ አምስት የሥራ ቀን ወስጥ ለሰጪው ጤና ተቋም ማድረስ ይኖርበታል፡፡
5. ሰጪው ጤና ተቋም ከተቀባዩ ጤና ተቋም የገቢ ደረሰኝ ሲደርሰው በመድሃኒት ማጋዘን ክፍለ ለዚሁ አገልግሎት በተዘጋጀ ፋይል ተደርጎ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 14. መድኃኒትን እጅ በእጅ ስለመሸጥ

1. በጤና ተቋም የእጅ በእጅ የመድሀኒት ሽያጭ **የሚከናወነው ለዚሁ ሲባል የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ** በሚያሳትመዉ እጅ በእጅ **የመድሀኒት ሽያጭ መሰብሰቢያ ደረሰኝ መሰረት** መሆን እና አሰራሩም **የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ** መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም ጤና ተቋም መድኃኒት ለተጠቃሚው መሸጥ ያለበት ከ**20%** ባልበለጠ የትርፍ ምጣኔ ሲሆን በመድሃኒት እደላ ላይ የተሰማራ የመድሃኒት ባለሙያ ሁሉ ወቅታዊ በሆነ የመድሃኒት ዋጋ መዘርዝር መሰረት ሽያጭ ያከናውናል፡፡
3. የመድኃኒቶች ወቅታዊ ዋጋ በዝርዝርና በግልፅ በሚታይ መልኩ የመድሃኒት ማደያ ክፍል አስተባባሪዎች ለታካሚው መለጠፍ አለበት፡፡
4. ማንኛውም የእጅ በእጅ የመድሀኒት ሽያጭ በችርቻሮ መሸጫ ዋጋ መሰረት በሶስት ቅጅ ተዘጋጅቶ ዋናው ለተገልጋዩ፣ የመጀመሪያው ቅጅ ለገንዘብ ተቀባይ፣ ሲሰጥ ሁለተኛው ቅጅ ደግሞ ከሰነዱ ጋር መቀመጥ አለበት፡፡
5. የእጅ በእጅ ሽያጬን ለማከናወን የመድሃኒት ማዘዣ ገምጋሚ የመድሀኒት ባለሙያ የታዘዘውን መድሃኒት ከታካሚው የጤና ሁኔታ እና አጠቃላይ  ጉዳዩችን ሙያዊ ግምገማ በማረጋገጥ ለሚገምተው የመድሃኒት ባለሙያ ያስተላልፋል፡፡
6. የእጅ በእጅ ሽያጬን ለማከናወን የተመደበው የመድሃኒት ባለሙያ ስለመድሃኒቱ ዋጋ  ለተጠቃሚው በቅድሚያ መግለጽ አለበት፡፡
7. ማንኛውም በመድሃኒት እደላ ላይ የተሰማራ የመድሃኒት ባለሙያ የሽያጭ ደረሰኞችን በስሙ መረከብ እና ለሶስተኛ ሰው አሳልፎ ሳይሰጥ መጠቀም አለበት፡፡
8. የእጅ በእጅ ሽያጬን ለማከናወን የተመደበው የመድኃኒት ባለሙያ በሽያጭ ደረሰኙ ላይ  የተመለከቱትን መረጃዎች በመሙላት ጠቅላላ ዋጋዉን በሽያጭ ደረሰኙ ላይ በቁጥርና በፊደል መጻፍና መፈረም አለበት፡፡
9. የመድሀኒት ሂሳብ ሰራተኛው የእለት የሽያጭ ማጠቃለያ ለዚሁ አላማ በተዘጋጀው ቅጽ መሰረት መስራት አለበት፡፡
10. ማንኛውም ጤና ተቋም ሽያጭ ለማከናወን ከፋርማሲ ሃላፊ ወቅታዊ የሆኑ የመድሀኒት ዋጋ ዝርዝር መረጃ ማግኘትና መጠቀም አለበት፡፡ በብልጫ ወይም በጉድለት የተሸጡ መድሀኒቶች ካሉ በመድሃኒት ሂሳብ ሰራተኛው በኩል በወቅቱ ተለይተው በእደላ ላይ ለተሰማራው ባለሙያው በመስጠት የእለቱ የሽያጭ ማጠቃለያ ቅፅ ላይ ይፈርማል ፡፡ይህም ሪፖርት በተቋሙ ኦዲተር ይረጋገጣል በብልጫ ወይም በጉድለት ለሚፈጠሩ ክፍተቶች እደላ ላይ የተሰማራው ባለሙያው ተጠያቂው ይሆናል፡፡በብልጫ የታየ ከሆነ ማብራሪያ የሚሰጥ ሲሆን በጉድለት የታየው ከሆነ ደግሞ የጎደለው ገንዘብ በወሩ መጨረሻ በአዲስ ደረሰኝ ተቆርጦ ገቢ ይደረጋል፡፡አፈጻጸሙም ቢሮው ባወጣጠው የጉድለትማካካሻ እና በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡
11. ገንዘብ ተቀባይ የሚቀርብለትን የእያንዳንዱን የሽያጭ ደረሰኝ የነጠላ እና የጠቅላላ ድምር የሂሳብ ስሌት በመስራት ልዩነት ሲኖር ለባለሙያው ተመላሽ ሆኖ እንዲስተካከል ማድርግ፣ ክፍያውን ሲቀበል ሶስቱም ቅጠሎች ላይ በፊርማው ማረጋገጥ አለበት ይህ ሳይሆን ሲቀር እና የሂሳብ ስሌት ስህተት ሲፈጠር ሁለቱም አካልቶች ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡የገንዘብ ተቀባይም የመድሀሃኒት ማዘዣ ወረቀት ላይ የደረሰኝ ቁጥር በማወራረስ ይፈርማል፡፡
12. ከላይ **በተራ ቁዓ C11 ላ** የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ገንዘብ ተቀባይ የፋይናንስ ደንቦችና አሰራሮችን ተከትለው መስራት እና ከቀን ሽያጭ ማጠቃለያው ጋር የተሰበሰበው ገንዘብን በማናበብ ሂሳቡ መግጠሙን ማገናዘብ እንዲሁም የሂሳብ ባለሙያው የሚሰራውን የዕለት ሽያጭ ማጠቃለያ እና ገንዘቡ የተቋሙ ዋና ገንዘብ ያዥ  በኩል ለባንክ ገብቶ የባልከ  ማረጋገጫ ስሊፑን ተመሳሳይ መሆኑን የፋርማሲ አካውታንቱ ማጠቃለያውን ያገናዝባል ለውሳኔም ያቀርባል፡፡

## 15. መድኃኒትን በዱቤ ወይም በመድን ሽፋን ስለመሸጥ

1. **ማንኛውም አካል በዱቤ ወይም በመድን ሽፋን የመድሀኒት አገልግሎት ሲጠይቅ ቀደም ብሎ ከጤና ተቋሙ ጋር የዱቤ አገልግሎት ውል የፈጸመ ወይም የጤና መድን ሽፋን ያለው መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡**
2. **የሶስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ሁሉም ተቋማት ከሁለት ሺ ብር ባልበለጠ ህክምና እንዲሰጡና በተቀመጠው መዝገብ መሰረት መዝግቦ በመያዝና በማደራጀት ይክፈለኝ ጥያቄ ለቢሮ አቅርቦ ተመላሽ ማድረግ**

ይቻላል (በትራንስፖርት ሚኒስትር የወጣው የተሸከርካሪ አደጋ ተጎጂ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1/2006.)

3. እያንዳንዱ ጤና ተቋም የጎዳና ተዳዳሪዎች፣ ከውጭ ሀገር ስደት ተመላሾች፣ ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት የታከሙበትን የመድኃኒት ዋጋ ሊከፍሉ ለማይችሉ ህሙማን የታደሉትን መድኃኒቶች በየደረጃው ከሚገኙ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤቶች እና የከተማ አስተዳደሩ በሚያስቀምጠው አሰራር እና ባለው የውል ስምምነት መሰረት ዝርዝር አገልግሎቱን በመላክ የአገልግሎት ዋጋ መቀበል ይኖርበታል፡፡
4. የተጠየቀው መድኃኒት ለህሙማኑ ከመታደሉ በፊት አገልግሎት ፈላጊ መ/ቤት በሚሰጠው ፎርማት መሰረት የታካሚው ስም፣ የጤና መድን ሽፋን ያለው ከሆነ የመድን መለያ ቁጥር፣ የካርድ ቁጥርና ሌሎች የህሙማኑን ማንነት የሚገልጹ መረጃዎችን መረጋገጥ አለበት፡፡
5. የመድህኒት ባለሙያው የመድህኒቱን ስም፣ አይነት፤ጥንካሬ ፣ ብዛት፣ የመድኃኒት የውስጥ መለያ ቁጥር፣ የታካሚው ካርድ ቁጥር፣ የመድን ሽፋን ካለው የመድን መለያ ቁጥር እና የችርቻሮ ጠቅላላ ዋጋ መመዝገብ እና ተጠቃሚው ወይም አስታማሚውን አስፈርሞ መስጠት አለበት፡፡
6. ማንኛውም የመድህኒት ሂሳብ ባለሙያ በየቀኑ በዱቤ ወይም በጤና መድን ሽፋን የተሸጡ መድህኒቶችን ከዱቤ ሽያጭ ቀሪ ጥራዝ ወይም ከመዝገቡ ላይ ለቅሞ የነጠላና የችርቻሮ ዋጋቸውን በማረጋገጥ የዱቤ ውሉን በፈጸመው አካል ወይም የጤና መድን ተቋም ስም ሂሳቡን በዱቤ ሽያጭ ማጠቃለያ ደረሰኝ መስራት አለበት፡፡
7. በዱቤ ወይም በመድን ሽፋን የተሸጡ መድሃኒቶች የሀኪም ማዘዣ ወረቀቶች የዱቤ ውል በገቡት ተቋማት እና የመድን ሽፋን በሰጠው ተቋም ስም ፋይል መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡
8. የመክፈል አቅም ለሌላቸዉና መንግስት የመድሃኒት ወጪያቸዉን ለሚሸፍንላቸዉ ታካሚዎች ጤና ተቋማት ለዱቤ ታካሚዎች የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ተከትለዉ ገንዘባቸዉን መሰብሰብ ይኖርባቸዋል፡፡
9. ጤና ተቋሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ላይ በተገለጸው መሰረት ውሉን ለፈጸመው አካል በማሳወቅ ገንዘቡ እንዲሰበሰብ ማድረግ አለበት::
10. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነዉ መድሃኒትን በጤና መድን ሽፋን መሸጥ ሌሎች የጤና መድን ሽፋን ደንቦችና መመሪያዎችን የተከተለ መሆን ይኖርበታል፡ በዚህም መሰረት ከአዲስ አበባ ውጭ ለሚመጡ የጤና መድህን አባላቶች በውላቸው መሰረት የመድሃኒት እደላው በሚከናወንበት ጊዜ ምዝገባው የእጅ በእጅ ደረሰኝ እና በጤና መድህን መመዝገቢያ ፎርማት መሰረት መከናወን ይኖርበታል፡፡ ለድንገተኛ ህሙማን የ24 ሰዓት አገልግሎት ቢሮው ባወጣው መመሪያ መሰርት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

16. ከክፍያ ነጻ የሆኑ መድኃኒቶች

1. የተጠየቀው መድሀኒት ለህሙማኑ ከመታደሉ በፊት በነጻ የሚታደሉ ስለመሆናቸው ማረጋገጥና የህሙማኑ ስም፣ የካርድ ቁጥርና ሌሎች የህሙማኑን ማንነት የሚገልጹ መረጃዎች ለዚሁ አላማ በተዘጋጀዉ መዝገብ ላይ መመዝገብ አለባቸው፡፡
2. የመድሀኒት ባለሙያው የመድሀኒቱን ስም፣ አይነት፣ ጥንካሬ፣ብዛት፤ የእሽግ መጠን፣ እና የውስጥ የመድኃኒት መለያ ቁጥሩን፣ የነጠላና የችርቻሮ ዋጋ መመዝገብና ታካሚውን ወይም አስታማሚውን አስፈርሞ መስጠት አለበት፡፡
3. ማንኛውም የመድሀኒት ባለሙያ በየቀኑ የሰራቸውን በነጻ የሚታደሉ የመድሀኒት ማዘዣዎችን መዝግቦና በቅደም ተከተላቸው አደራጅቶ ለፋርማሲ ሂሳብ ባለሙያ ማስረከብ ይኖርበታል፡፡
4. የመድሀኒት ክፍል ሂሳብ ባለሙያ በየቀኑ በነጻ የታደሉትን መድሀኒቶች ከመዝገቡ ላይ ለቅሞ የችርቻሮ እና አጠቃላይ ዋጋቸውን በማረጋገጥ ሪፖርት በሚቀርብለት አካል ስም በማደራጀት በነጻ ስለታደሉት መድሀኒቶች ወራዊ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ማቅረብ አለበት፡፡
5. በከተማችን የወረርሽኝ ፣ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ አደጋዎች ሲከሰቱ አገልግሎቱ በነፃ ተሰጥቶ መረጃው በክፊያ ነጻ መዝገብ ላይ መዝግቦ መያዝና ማደራጀት፤የአገልግሎት ክፍያውን ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ክፍያ መጠየቅ፣ አለበት፡፡
6. ያለክፍያ የሚሰጡ አገልግሎቶች ከፍለው ለሚታከሙ ፣ለዱቤ ታካሚዎች እና ለመድህን ሽፋን ተጠቃሚዎች በተመሳሳይ ከክፍያ ነፃ ይሰጣሉ፡፡የተሰጠውንም አገልግሎት በመመሪያው መሰርት የሚመለከተውን አካል ክፍያ ይጠይቃል፡፡

## ክፍል አራት

## <u>የመድሀኒት አጠቃቀም ስርዓት</u>

### 17. ስለ መድሀኒት አስተዛዘዝ

ስለ መድሀኒት አስተዛዘዝ

1. በጤና ተቋም የሚሰጠ ህክምና በሀገር አቀፍ ደረጃ በየደረጃው ስራ ላይ እንዲውል በሚመለከተው አካል በወጣው የህክምና መመሪያ መሰረት መሆን ይኖርበታል፡፡
2. በጤና ተቋም ለታካሚዎች የሚታዘዙ መድሃኒቶች አሳማኝ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በተቋሙ የመድሃኒት ማዘርዝር ወስጥ የተካተቱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
3. መድሃኒት የሚታዘዘው የሙያ ደረጃው በሚፈቅደለት ባለሙያ ብቻ መሆን አለበት፡፡
4. ማንኛውም ጤና ተቋም በባለሙያዎቹ የሚታዘዙ መድሃኒቶች የታካሚውን ያለፈ የህክምና፤ የመድሃኒት አወሳሰድና አለርጂ ታሪክ፤ የአመጋገብ ስርዓትና የስራ ሁኔታ ማእከል ያደረገና ታካሚውን ባሳተፈ መልኩ መካናወኑን ሚረጋገጥ አለበት፡፡ ማንኛውም የመድሀኒት የጎንዮሽ ጉዳት ካለ በተቀመጠው ቅፅ መሰረት ለተጠሪው ክፍል ሪፖረተ የማድረግ ሃላፊነት/ግዴታ አለበት፡፡
5. መድሀኒት እንዲያዝ የተፈቀደለት ባለሙያ የመድሀኒት ማዘዣውን እየፈረመ መውሰድ አለበት.
6. በማንኛውም ጤና ተቋም መድሃኒት ሲታዘዝ አገር አቀፉን የመድሀኒት ማዘዣ መሆን ይኖርበታል፡፡
7. ልዩ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒቶች ለዚሁ ተግባር በሚመለከተው አካል በተዘጋጅት ማዘዣ ወረቀቶች ብቻ መታዘዝ አለባቸው፡
8. የመድሀኒትና የህክምና መማክርት(ዲቲሲ). በመድሀኒት፤ምግብ ጤና ቁጥጥር ባለስልጣን ባወጣው አግባብት ያለው የመድሀኒት አጠቃቀም መመሪያ መሰረት መሆን አለበት
9. መድሃኒቶች በጽንሰ ስም ብቻ መታዘዝ አለባቸው፡
10. ማንኛውም የጤና ባለሙያ በመድሃኒት ማዘዣ የሚሰጡ መድሃኒቶችን ለራሱ ማዘዝ አይችልም፡

### 18. ስለመድሃኒት እደላ

1. ***በመድሀኒት፤ምግብ ጤና ቁጥጥር ባለስልጣን ባወጣው አግባብነት ያለው የመድሃኒት እደላ መመርያ መሰረት መድሃኒቶች ለታካሚ ወይም ለደንበኛ ከመታደላቸው በፊት የመድሃኒት ማዘዣ ወረቀቱ ህጋዊነትና አስፈላጊ መረጃዎች መሟላታቸው መረፋቶዓ ፤ያልተሟላ ከሆነ እንዲሟላ ካዘዘው አካል ጋር በመነጋገር ማስተካከያ በማድረግ መዝግቦ መያዝ፤ሪፖርት ማድረግ ፤የተለያዩ ባለሙያዎች በተገኙበት በመወያየት የጋራ ማትረፅ ፤የሌሉ መድሃኒቶች ከሆኑ የሚተካኩበት ሁኔታ እንዲመቻች ማድረግ ነገር ግን ፈፅመው በተቋሙ ከሌሉ ወይም ካልተገኙ በሀኪም ብቻ ተጽፈው ከውጭ እንዲገዙ መላክ አለባቸው።***
2. ***በአገር አቀፉ የጤና ተቋማት የአገልግሎት አሰጣዓ □ረጽ መሰረት ለተከሚ የሚታ□ለዉ መድሃኒት ማሸጊያ መያዝ ያለበት መረጃ፡ የተቋሙ ስም፤ የታካሚው ስም፤የይዘት መጠን፤ብዛት፤የመድሀኒቱ አወሳሰድ፤ያወሳሰድ ጊዜ እና ቀን ፤ያወሳሰድ ሁኔታ የመድሃኒት የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ፤የአቀማመጥ ሁኔታ ፤ከአመጋገብ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በፅሁፍ መስጠት፡ አለበት።***
3. ***የኢትዮጵያ የምግብ ፤የመድሀኒት እና ጤና ክብካቤ ቁጥጥር ባለስልጣን ባወጣው የመድሀኒት መዘዣመመሪያ መሰረት ማዘዣው ከተጻፈበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ወር የሚያገለግል ሲሆን ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድሀኒቶች ማዘዣ ግን በ15 ቀን ውስጥ መስተናገድ አለባቸው፡፡***
4. ***□ሚታደለውን እያንዳንዱን መድሃኒት በተመለከተ ስለአወሳሰዱ፤ ተጓዳኝ ችግሮቹ፣ ከምግብና ሌሎች መድሃኒቶች ጋር ስላለው ተቃርኖ፤ የአቀማመጥ ሁኔታና የመሳሰሉት አስፈላጊ መረጃዎች ለህሙማን መንገር ብሎም የታካሚውን ሚስጥር መጠበቅ አለበት፡፡***

5. የመድሃኒቶች እ□ላ የሚከናወነዉ የሙያ ደረጃው በሚፈቅድለት ባለሙያ ብቻ መሆን አለበት፡፡
6. ልዩ ቁጥጥር ለሚያስፈልጋቸዉም የመድሃኒት እና ማዘዣ ወረቀቶች የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ባወጣዉ መመሪያ መሰረት በአግባቡ ፋይል ተደርገው ለተወሰነላቸዉ ጊዜ መቀመጥና መወገድ አለባቸው፡፡
7. ለተከሚ □ሚተ□□ መድሃኒቶችን □አና በተቋሙ ያልተገኙ መድሃኒቶችን በስራ ላይ ባለው የመረጃ አያያዝ ምዝገባ ስርአት(መዝገብ) ላይ በመመዝገብ መረጃችን ማጠናከር አለበት፡፡
8. ከላይ በተራ ቁጥር7 ላይ የተጠቀሰው እእአንደተጠበቀ ሆኖ መድሃኒት በተቋሙ ውስጥ ያለመኖሩ ከተረጋገጠ የመድሃኒት ዕደላ ባለሙያው መድሃኒት ማዘዣው ከጀርባው ላይ ስሙን :ፊርማውን ቀንና ማህተም አረጋግጦ ለተገልጋዩ መስጠት አለበት፡፡
9. በአጠቃላይ የመድሃኒት እደላ ስርዓትን በተመለከተ በዚህ አንቀጽ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ጤና ተቋማት ሀገር አቀፉን የጤና ተቋማት ደረጃ በተከተለ መልኩ ማከናወን አለባቸው፡፡
10. የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በቢሮው በተቀመጠላቸው ወሰን መሰረት አንደ አንድ ፋርማሲ አገልግሎት የመድሃኒት ዕደላ ስራ ማከራት ይችላሉ፡፡

## 19. የመድሀኒት መረጃ አገልግሎት

1. በጤና ተቋም ውስጥ ለጤና ባለሙያዎች የመድሀኒት መረጃ አገልግሎት የሚሰጥ እና ህሙማን ስለመድሀኒት አጠቃቀም የሚያስተምር ደረጃዎችን በጠበቁ ወቅታዊ የመረጃ ምንጮች የተደራጀ የመድሀኒት መረጃ ማዕከል ማቋቋም አለበት
2. ማዕከሉ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በአግባቡ መመዝገብና ፋይል ማድረግ ብሎም ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መላክ አይኖርበታል፡፡
3. የመረጃ ማዕከሉ ከመድሃኒት አጠቃቀም ጋር የተያያዙ የተጠበቁም ሆነ ያልተጠበቁ እና ከበድ ያሉ የመድሃኒት ጉዳቶችን በኢትዮጵያ የምግብ፤ የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት ሪፖርት እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
4. የመረጃ ማዕከሉ የበሽታ አምጭ ተህዋስያን ከጸረ-ተህዋስያን መድሃኒቶች ጋር መላመድን ለመከላከልና ለመቆጣጠር መረጃዎችን ያጠናቅራል፤ በመመሪያ እንዲመራ ያደርጋል፤ ጥናቶችን ጸስተባብራል፤ መረጃዎቹ ስራ ላይ እንዲዉሉ ያደርጋል፡፡
5. የጤና ተቋሙ መድሃኒትና ህክምና መማክርት ኮሚቴ ድጋፍ ያደርጋል፤ችግር ፈቺ የሆኑ የመድሃኒት አቅርቦትና አገልግሎት አስመልክቶ ጥናቶችን በማድረግ መፍትሄዎችን ያስቀምጣል፡፡
6. አዳዲስ ወቅታዊ የህክምና አማራጮችን መረጃ በማጠናቀር ለሙያተኛው ያሳውቃል፡፡
7. ትምህርታዊ ርእሶችን ከዲቲደሲ ጋር በጋራ በመምረጥ ለታካሚዎችና ለባለሙያዎች ተከታታይ ትምህርቶቸን ይሰጣል፡፡

## 20. የክሊኒካል ፋርማሲ አገልግሎት

1. አግባባዊ የመድሃኒት አጠቃቀምን በማስፈን ተኝተው የሚታከሙ ህሙማን ከህክምናቸው የሚጠበቀው ውጤት ላይ እንዲደርሱ በጤና ተቋማት ፋርማሲስቶች በህክምና አሰጣጥ ሂደቱ ቀዓተኛ ተሳታፊ የሚሆኑበት የክሊኒካል ፋርማሲ አገልግሎት በሆስፒታል ተፅባራዊ መረፅ አለበት፡፡
2. የክሊኒካል ፋርማሲ አገልግሎትን ውጤታማ በሆነ ደረጃ ለህሙማን ለመስጠትእአንዲያመች ታካሚው የህክምና መረጃ ይህን አገልግሎት ለሚሰጡ ፋርማሲስቶች ክፍት መሆን አለበት፡፡
3. ፋርማሲስቶቸ ስለእያንዳንዱ ታካሚ መድሃኒት ነክ መረጃዎች የሚያሰፍሩበት እና ክትትል የሚያደርጉበት ፎርም ተዘጋጅቶ የታካሚው የህክምና ካርድ አካል ሆኖ ስራ ላይ መዋል አለበት፡፡ ማንኛውም የመድሀኒት የጎንዮሽ ጉዳት ካለ በተቀመጠው ቅፅ መሰረት ለተጠሪው ክፍል ሪፖረተ የማድረግ ሃላፊነት/ግዴታ አለበት
4. ተኝተው ለሚታከሙ ህሙማን በሚሰጠው የህክምና አገልግሎት በመድሃኒት መረጣ፤ በህሙማን ክትትል፤ ለጤና ባለሙያዎች እና ለህሙማን በመድሃኒት አጠቃቀም ዙሪያ መረጃ እና ምክር በመስጠት መሳተፍ አለባቸው፡፡ለነዚህ ህሙማን የሚታደለው መድሀኒት ለ 24 ሰዓት አገልግሎት የሚውል ብቻ መሆን አለበት፡፡
5. የጤና ቡድኑ ተኝተው ስለሚታከሙ ህሙማን ውይይት በሚያደርግባቸው መድረኮች እና በየዋርዶቹ የህሙማንን የህክምና ሁኔታ ለመፈተሽ በሚደረጉ የህሙማን ጉብኝቶች ላይ የክሊኒክል ፋርማሲ ባለሙያዎች መሳተፍ በተጨማሪም የክሊኒካል ፋርማሲስት በቡድን በመሆንን የህሙማንን ሁኔታ መከታተልና ትምህርት መስጠት አለባቸው
6. የክሊኒክል ፋርማሲ ባለሙያዎች ተኝተው ስለሚታከሙ ህሙማን ተከታታይነት ያለው መረጃ በመጸዝ ከመድሃኒት አጠቃቀምና የህክምና ውጤት ጋር በተያያዘ የቅርብ ክትትል ማድረግና ተገቢውን ምክር ለባለሙያዎችና ለህሙማን መስጠት አለባቸው፡፡
7. በባለሙያዎች መካከል የመረጃ ቅብብሎሽ እንዲኖር በማድረግ የህክምና አገልግሎቱ ቀጣይነት እንዲኖረው ታካሚዎች ወደ ሌላ ጤና ተቋም ሲዛወሩ ወይም ህክምናቸውን ጨርሰው ሲወጡ መድሃኒት ነክ መረጃዎች ለህሙማኑ ሊሰጧቸው ይገባል፡፡

## 21. የመድሐኒት ቅመማ አገልግሎት

1. የመድሃኒት ቅመማ ስራ የሚሰራ ተቋም በምግብ፣ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ዝቅተኛ ማስፈርት ማሟላት ይገባዋል፣
2. የሚቀመሙ መድሐኒቶች የየራሳቸው የሆነ የቅመማ አሰራር አዘገጃጀት ቅደም ተከተል መመሪያ ማዘጋጀትና መከተል አለባቸው፤
3. የተቀመመዉን መድሀኒት አግባብነት ባለው መዝገብ ላይ መዝግቦ አገልግሎቱን ማስጠትና አለበት
4. የተቀመመዉን መድሀኒት ለታካሚ ሲሰጥ ቢያንስ የሚከተሉትን ሚጃዎች በፅሁፍ ማስጠት አለበት ፡፡
   ሀ. የመድሐኒቱ ስም
   ለ. የተመረተበት ቀን
   ሐ. የምርቱ መለያ ቁጥር
   መ. የጤና ተቋሙ ስም
   ሠ. የሚጠቀሙት ንጥረ-ነገር ከእነ ምርት መለያ ቁጥር
   ረ. የአጠቃቀም ሁኔታ
   ሰ. የቀመመው ባለሙያ ስም
   ሸ. የአገልግሎት ጊዜ እና አቀማመጥ ሁኔታ

5. የጤና ተቋሙ የቅመማ አገልግሎት ክፍያን በተመለከተ ግምት ወስጥ መግበት ያለባቸው የያንዳንዱ መድሀኒት ግብአቶች ዋጋ ግምት ወስጥ ያስገባ መሆን አለበት፤ አሰራሩን በሮው ክትትል ያደርግበታል፡፡

## 22. የመድኃኒት እና ሕክምና ኮሚቴ

1. አመታዊ እቅድ ያዘጋጃል ከዋና የተቋሙ እቅድ ላይ እንዲካተት ደርጋል አንድ ኮፒ ከኮሚቴው ክፍል ይቀመጣል አንድ ኮፒ ፋይል ያደርጋል፡፡
2. የኮሚቴው አባላትን በደብዳቤ ያስወቃል የመግባቢያ ሰነድ ተዘጋጅቶ የተቋሙ ሁሉንም ባለሙያ እንዲያወቁት ያደርጋል ፤በተቀመተው የግንኙነት ጊዜ ማለትም በየሁለት ወሩ አንድ ጊዜ ወይም በአመት ስድስት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ የደርጋል ፡በተሰጠው ኃላፊነት ወሳኔዎች እያሳለፈ እንደ አሰፈላጊነቱ ለሜኔጅመንት አቅርቦ ያጸድቃል፡፡

4. አግባባዊ ለሆነ መድሐኒት አቅርቦትና አገልግሎት ተቋሚዊ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች ማዘጋጀት አለበት፡፡
5. ተቋሚዊ የመድሐኒት ዝርዝር እና የሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ወይም ትሪትመንት ጋይድ ላይን ያዘጋጃል አንደ አስፈላጊነቱ ወቅታዊነቱንም የስጠብቃል፡፡
6. በመድሐኒት አጠቃቀም ስርዓት ዙርያ ያሉትን ሂደቶች በሳይንሳዊ መንገድ ጥናቶችን ያደርጋል እንደ አስፈላጊነቱም ትክክለኛ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፡፡
7. ያለተፈለገ ወይም ያልታሰቡ የመድሐኒት ክስተት ክትትል እና ሪፖርት የሚደረግበት አሰራር ይተገብራል፡፡
8. በተዘጋጀው የመድሐኒት ዝርዝር መሰረት በተለይም ልዩ የክትትል እና ቁጥጥር ሂደት
9. በሚያስፈልጋቸው መድሐኒቶች ናርኮቲክስ፤ ሳይኮትሮፒክ ከፍተኛ ጸረ-ምረዛ ወዘተ ይለያል የእርምት እርምጃ ይወስዳል ፡፡
10. የመድሐኒት ሚጃ ማዕከል አገልግሎት፣ የክሊኒካል ፋርማሲ ቅመማ ፤ ኤ ፒ ቲ ኤ ስ ያጠናክራል፤ የመድሐኒት አጠቃቀም ስርዓት ይተገብራል፡፡

## 23. ረጅም ጊዜ ለሚታከሙ ህሙማን የሚሰጥ የፋርማሲ አገልግሎት

1. **በተመላላሽ ህክምና ተላላፊና ተላላፊ ባልሆኑ ህመሞች ረፀም ቿ□ ለሚታከሙ ህሙማን ማለትም የቲቢ፤ ኤች አይ ቪ፤ ስኳር፤ ደም ግፊት፤ ልብ፤ ካንሰር፤ አስም፤ የአእምሮ ጤና ለመሳሰሉት ህሙማን ፋርማሲስቶች ስለህሙማኑ ተከታታይነት ጸለዉ መረጽ በመጸ□ ተፃቢ**

የክትትልና □ም□ር አገልፅሎት መስጠት አለባቸው::

2. የህክምና አገልግሎቱ ቀጣይነት እንዲኖረው ታካሚዎች ወደ ሌላ ጤና ተቋም ሲዛወሩ ለህሙማኑ ዋና ዋና መድሃኒት ነክ መረጃዎች ሊሰጧቸው ይገባል::
3. የህሙማን መድሃኒት ነክ መረጃ በአግባቡ መያዝ የሚያስችል ፎርም ተዘጋጅቶ ስራ ላይ መዋል አለበት፡፡ማንኛውም የመድሀኒት የጎንዮሽ ጉዳት ካለ በተቀመጠው ቅፅ መሰረት ለተጠሪው ክፍል ሪፖረተ የማድረግ ሃላፊነት/ግዴታ አለበት አባሪ/እዝል
4. ለረጅም ጊዜ መድሃኒት የሚወስዱ ታካሚዎች የፋርማሲ አገልግሎት የሚሰጡ ፋርማሲስቶቸ ተገቢውን ስልጠና ማግኘት አለባቸው፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

### የመድሀኒት ቆጠራ ኦዲተና ሪፖርት ስለማድረግ

**24. የመደሀኒት ቆጠራ**

1. ጤና ተቋማት በመድኃኒት መጋዘን የሚገኙ መድሀኒቶችን በመድሃኒት መቁጠሪያ ቅጽ በተዘጋጀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ቆጠራ ማከናወን አለባቸው፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንዳለ ሆኖ እነደ አስፈላጊነቱ ማንኛውም የጤና ተቋም በየሩብ አመቱ ወይም ድንገተኛ የመድሃኒት ቆጠራ ሊያካሂዱ ይችላሉ፡፡
3. ጤና ተቋማት በመድኃኒት ማደያ ክፍሎች የሚገኙ መድሀኒቶችን በመድሃኒት መቁጠሪያ ቅጽ በወር አንድ ጊዜ ቆጠራ ማካሄድ አለባቸው፡፡
4. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2 እና 3 የተገለጸው የቆጠራ ውጤት ከመድሃኒት መቆጣጠሪያ መዝገቦች (ቢን ካርድ፣ ስቶክ ካርድና ሶፍት ዌር) እና ከሂሳብ ሪፖርት ጋር ተገናዝቦ ለጤና ተቋሙ ሃላፊ ሪፖርት መደረግ አለበት፡
5.በመድኃኒት ማደያ ክፍሎች የሚገኙ መድኃኒቶች በወር አንድ ጊዜ ቆጠራ ማካሄድ አለባቸው፡፡

## 25. የገንዘብ አሰባሰብና የሒሳብ ሪፖርት አቀራረብ ስርዓት

1. በጤና ተቋማት በየቀኑ በተለያዩ የመድሃኒት ማደያ ክፍሎች ለህሙማን በክፍያ፣ በዱቤ፣ በነፃ ሽያጭ እና ያለክፍያ የታደሉ መድኃኒቶች በባለሙያ ስም፣ በታካሚ ብዛት፣ በመድኃኒት ብዛት እና በዋጋ ተለይቶ ወደ ዕለት ሽያጭ ማጠቃላያ ቅፅ መመዝገብ አለበት፤ ከዋጋ በላይ እና በታች የተሰበሰበ ገንዘብ ተለይቶ ይመዘግባል እንዲሁም ሪፖርት ያደርጋል፡፡

2. በጤና ተቋማት በየዕለቱ የተሰበሰበው ገንዘብ ወደ ባንክ ወይም ወደ ረዳት ፋይናንስ ኦፊሰር

ለማስተላለፍ መሂ-3 ሰነድ ይዘጋጃል፤ የገንዘቡን መጠን ከባንክ ደረሰኝ እና ከማጠቃለያ ሰነድ ጋር አገናዝቦ ካረጋገጠ በኋላ ወደ ሰነድ ክፍል እንዲመለስ መደረግ አለበት፡፡

3.ማንኛውም የፋርማሲ ክፍል ሂሳብ ባለሙያ በወሩ መጀመሪያ ቀን የነበረውን ድምር

የመድሀኒት ዋጋ እና በወሩ ውስጥ ወደ ክፍሉ እና ጤና ተቋሙ የገባውን ጠቅላላ የመድሀኒት ዋጋ በመደመር፣ ከዚሁ ላይ በወሩ ውስጥ የተሸጠውን ድምር የመድሀኒት ዋጋ እና ጥቅም ላይ የማይውሉ መድሀኒቶችን በመለየት፣ ከወጭ ቀሪ ያለውን መድሀኒት ዋጋ በተመለከተ በሚዘጋጀው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ መሰረት ለጤና ተቋሙ ሃላፊ ሪፖርት ማድረግ አለበት

4. በየወሩ የተከናወኑ የፋይናንስ እና የመድኃኒት አገልግሎት ተግባራትን የሚያሳዩ መረጃዎችን ማለትም የዕለት ሽያጭ ማጠቃላያዎችን ፣ ሞዴል 22/ጤ፣ የቆጠራ ሪፖርት፣ ወደ ሌላ ክፍልና ጤና ተቋም የተላለፉ መድኃኒቶችን፣ የአገልግሎት ጊዜአቸው ያለፈባቸውን እና የተበላሹ መድኃኒቶችን ዝርዝር በማደራጀትና በግባትነት በመጠቀም ወርሃዊ የፋይናንስ እና የመድሃኒት አገልግሎት አሰጣጥ ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡

## 26. የአገልግሎት አሰጣጥ ሪፖርት ስለማቅረብ

1. የፋርማሲ ክፍሉ በመድኃኒት መዘርዝሩ የተካተቱን ከማለቃቸዉ በፊት ማሳወቂ እንደተጠበቀ ሆኖ በክምችት የሌሉ መድሀኒቶችን በየወሩ ለተቋሙ ኃላፊ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የጤና ተቋም ያቀረበው መድሃኒት የህብረተሰቡን የመግዛት ፍላጎትና አቅም ያገናዘበ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. ማንኛውም የፋርማሲ ክፍል የሂሳብ ባለሙያ በእያንዳንዱ የመድሃኒት ባለሙያ የተስተናገደዉን የተገልጋይ ቁጥር፣ የተሰጠውን አገልገሎት በአይነት ጠቅሶ በወሩ መጨረሻ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
4. የጤና ተቋማት የፋርማሲ ክፍል የክፍሉን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ቢሮ በሚያዘጋጀዉ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ መሰረት ሪፖርት መላክ አለበት፡፡
5. ማንኛውም የጤና ተቋም ስለ መድኃኒት አገልግሎት የሚፈለጉ ሪፖርቶችን በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱ ፣ በየግማሽ አመቱ እና በየአመቱ የማጠቃለያ ሪፖርት ሰርቶ የማጠናከሪያ እና የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

## 27. ግምገማ እና ኦዲት ስለማስደረግ

1. በጤና ተቋሙ ውስጥ የሚከናወኑ የመድኃኒት አገልግሎት አሰጣጥ አግባብነት ማለትም የመድኃኒት ማዘዣዎችን ትክክለኛነት፣ የተለዩ ከመድኃኒት ጋር የተያያዙ የህክምና ችግሮች፣ ለታካሚዎች የሚሰጠውን የምክር አገልግሎት፣ የመድኃኒት አጠቀቀም እና የታካሚዎችን

እርካታ በተመለከተ በመድኃኒትና ህክምና ኮሚቴ እና ጥራት ኮሚቴ የጋራ ትብብር ቢያንስ በሩብ ዓመት በማስገምገም ሪፖርት የማዘጋጀትና የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በውስጥ ወይም በውጭ ኦዲተሮች የመድኃኒት አገልግሎት አሰጣጥ ክዋኔ ኦዲት ያስደርጋል፡፡

3. ማንኛውም የጤና ተቋም በተለያዩ ክፍሎቹ የሚከናወነውን የመድሃኒት አቅርቦት እና ስርጭት እንዲሁም የአገልፅሎት አሰጣጡን በሚመለከት በዉስዓ ኦቴተር በሩብ መቱ እና በዉ ኦቴተር ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ኦዲት ያስደርጋሉ:: የኦዲት ሪፖርቱ ለተቋሙ ከፍተኛ አመራር ወይም ቦርድ በማቅረብ ተገቢው ርምጽ ንዲወሰድ ያደርጋሉ::

4. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጤና ተቋሙ በማንኛውም ጊዜ ኦዲት ማስደረግ ይችላል፡፡

5. በማንኛውም ጤና ተቋም የኦዲት ስራው ተጠናቆ ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሪፖረት ሲቀርብለት ውጤቱን መሰረት አድርጎ አስፈላጊውን እርምጃ በወቅቱ መውሰድ አለበት፡፡

6. በተፈቀደው የጉድለት ተጋላጭነት ማካካሻ ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት በየሶስት ወሩ በመጋዘንና በመድሃኒት ማደያ ክፍሎች ጉድለት መኖርና አለመኖሩን በኦዲተር እያስመረመረ የጉድለት ማካካሻ ክፍያ እንዲፈም ያደርጋል፡፡

### 28. ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶችን ሪፖርት ስለማድረግ

1. ማንኛውም የተቋሙ የፋርማሲ ባለሙያ በሌሎች ህጎች ላይ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ጥቅም ላይ የማይውሉ መድሀኒቶችን የመድሃኒቱን ስም፣ መጠን፣ የምርት መለያ ቁጥር፣ የአገልግሎት ማብቂያ ቀን፣ የአምራች ፋብሪካ ስም፣ የነጠላ ዋጋ እና የችርቻሮ ዋጋ በመመዝገብ በየወሩ ለፋርማሲ ክፍል ሂሳብ ሰራተኛ እና ፋርማሲ አገልግሎት ኃላፊ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
2. የተቋሙ የፋርማሲ ክፍል ሂሳብ ሰራተኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱትን መድሀኒቶች በወርሃዊ የሂሳብ ሪፖርት ለፋርማሲ አገልግሎት ኃላፊ እና ለፋይናንስ ኃላፊ ሪፖርት ማድረግ አለበት

### 29.ጥቅም ላይ የማይውሉ መድሃኒቶችን ስለማስወገድ

1. በጤና ተቋማት መድሃኒት መጋዘንና በተለያዩ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች የሚገኙ ጥቅም ላይ የማይውሉ መድሃኒቶች ለዚሁ ተግባር ተብሎ በተዘጋጀው ቅጽ መሰረት መመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡

2. ጥቅም ላይ የማይውሉ መድሃኒቶች እስከሚወገዱ ድረስ ከስድስት ወር ላልበለጠ ጊዜ እንደ የባህሪያቸው ተለይተው መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡

3. በበጀት አመቱ ጥቅም ላይ የማይውሉ መድሃኒቶች አጠቃላይ ለጤና ተቋሙ ከቀረበው መድሃኒት አንጻር የብክነት መጠን በገንዘብ መሰላት ያለበት ሲሆን ይህም በእርዳታ ለተገኙና በበጀት ለተገኙ መድሃኒቶች ተለያይተው መሰራት ይኖርበታል፡፡

4. ጥቅም ላይ የማይውሉ መድሃኒቶች መረጃ አያያዝና አወጋገድ በተመለከተ ስልጣን በተሰጠው አካል ባወጣው መመሪያ መሰረት መከናወን አለበት፡፡

**30. ጥቅም ላይ የዋሉና አገልግሎት የማይሰጡ የመድሃኒት ሰነዶች ስለማስወገድ**

1.ጥቅም ላይ የዋሉና ከአገልግሎት ዉጪ የሆኑ የመድኒት ገቢና ወጪ ሰነዶች እስከሚወገዱ ድረስ ሰነዶች ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ መቀመጥ እንዳለባቸው የተጠበቀ ሆኖ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መስሪያቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 6/2003 እና የመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 10/2003 መሰረት ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡

2. አገልግሎት ላይ የዋሉና ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ የመደበኛ መድሃኒት ማዘዣ ወረቀቶች መረጃ አያያዝና አወጋገድ በተመለከተ ስልጣን በተሰጠው አካል ባወጣው መመሪያ መሰረት መከናወን አለበት፡፡

3. አገልግሎት ላይ የዋሉና ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት ማዘዣ ወረቀቶች መረጃ አያያዝና አወጋገድ በተመለከተ ስልጣን በተሰጠው አካል ባወጣው መመሪያ መሰረት መከናወን አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

31.ጥፋቶችና ቅጣቶች

ማንኛውም ሰው ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ካላከበረ ወይም ተላልፎ ከተገኘ በከተማ አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ እንዲሁም በሌሎች የአገሪቱ ሕጐች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

32.የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም መተባበር አለበት፤

33.መመሪያ ስለማሻሻል

እንደአስፈላጊነቱ ይህ መመሪያ ሊሻሻል ይችላላል፤

34.ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም መመሪያዎች ወይም ተለመዱ አሰራሮች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፤

35.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጥቅምት.....ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ጥቅምት/2011

ዶ/ር ዮሐንስ ጫላ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ